| VI | 2367 | 2593 | 2820 | 3098 | 3369 | 3641 | 3973 | 4269 | 4565 | 4928 | 5263 |
| VII | 3098 | 3369 | 3641 | 3973 | 4269 | 4565 | 4928 | 5263 | 5598 | 6008 | 6389 |
| VIII | 3973 | 4269 | 4565 | 4928 | 5263 | 5598 | 6008 | 6389 | 6770 | 7237 | 7697 |
| IX | 4928 | 5263 | 5598 | 6008 | 6389 | 6770 | 7237 | 7697 | 8120 | 8640 | 9131 |
| X | 6008 | 6389 | 6770 | 7237 | 7697 | 8120 | 8640 | 9131 | 9622 | 10223 | 10792 |
| XI | 7237 | 7697 | 8120 | 8640 | 9131 | 9622 | 10223 | 10792 | 11283 | 11884 | 12453 |
| XII | 8640 | 9131 | 9622 | 10223 | 10792 | 11283 | 11884 | 12453 | 12944 | 13545 | 14114 |

www.abyssinialaw.com


# ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ
# የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ

## ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ
## የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መበል 18 ዓመት ቑ. 16 መቐለ 69/2003 ዓ.ም

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝወፀ

18ኛ ዓመት ቁ. 16 መቐለ 69/2003 ዓ/ም


**ቑፅሪ ደንቢ 69/2003**

**ተመሓይሹ ዝወፀ ደንቢ ምምሕዳር ፋይናንስ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ**

ቤት ምኽሪ ስራሕ ፈፃሚ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ብመሰረት ምምሕዳር ፋይናንስ ቑፅሪ ኣዋጅ 173/2002 ዓንቀፅ 63/1/እዚ ደንቢ'ዚ ኣውፂኡ ኣሎ፡፡

**ክፍሊ ሓደ**
**ሓፈሻዊ**

1. **ሓፂር ርእሲ**

እዚ ደንቢ "ደንቢ ምምሕዳር ፋይናንስ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ቑፅሪ ደንቢ 69/2003 ዓ.ም" ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል።

2. **ትርጉም፡-**

ኣብ'ዚ ደንቢ ውሽጢ፡-

1. "ቅድመ ክፍሊት" ማለት ተቐባሊ ድሕሪ ዝተወሰነ እዋን ዘወራርዶ ክፍሊትን ናይ ዋጋ ልውውጥ ዘይተገበረሉን እንትኾውን ውዕሊ መሰረት ብምግባር ኣብ'ቲ ውዕሊ ዝተቐመጠ ግቡእ ቅድሚ ምውድኡ በብ ብርኩ ዝግበር ክፍሊት ኣይሓውስን።
2. "ወፃኢ ካፒታል" ማለት፣

ሀ/ መንገድታትን ህንፃታትን ወይ ካልኦት ህንፀታት ከይሓወሰ መሬት ንመሓዝ ፣ መሊስካ ንምሓዝ፣ ንምምሕያሽ ወይ ንምድላው፣

**ደንብ ቁጥር 69/2003**

**ተሻሽሎ የወጣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ**

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 173/2002 አንቀጽ 63/1/መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 69/2003 ዓ.ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "የቅድሚያ ክፍያ" ማለት የዋጋ ልውውጥ ያልተደረገበት እና ተቀባዩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚያወራርደው ክፍያ ሲሆን ውልን መሰረት በማድረግ በውሉ የተመለከተው ግዴታ ከመጠናቀቁ በፊት በየደረጃው የሚደረግን ክፍያ አይጨምርም።
2. "የካፒታል ወጪ"ማለት፣

ሀ/ መንገዶችን ሕንጻዎችን ወይም ሌሎች ግንባታዎችን ሳይጨምር መሬትን ለመያዝ፣ መልሶ ለመያዝ፣ ለማሻሻል ወይም ለማዘጋጀት፣

ለ/ መንገድታትን ህንፃታትን ወይ ድማ ካልኦት ንምሓዝ፣ንምስራሕን ንምድላው ወይ ድማ ንምምሕያሽ።

ሐ/ ዝንቀሳቐሱ ወይ ዘይንቀሳቐሱ ትካላትን፣ መሳርሕታትን መገልገሊታት፣ ተሽከርከርቲ ኣውሮፕላናትን ዝኣመሰሉን ንምሓዝ፣ ንምትካል ወይ ንምትካእ ።

መ/ ኣብ'ዚ ንኡስ ዓንቀፅ ካብ ፊደል ሀ-ሐ ዝተዘርዘሩ ንምፍፃም ወይ ድማ ስራሕቲ ኢንቨስትመንት ንምሓዝ ንዝተገበረ ወይ ድማ ንዝግበር ወፃኢ ንኽውዕል ንዝኾነ ሰብ ሓገዝ ቅድመ ክፍሊት ወይ ድማ ካልእ ዓይነት ድጋፍ ገንዘብ ምሃብ።

ረ. ሕጋዊ ሰብነት ኣብ ዝተዋህቦም ትካላት ንግዲ ውሽጢ ካፒታል ብፅሒት ኣክስዮን ወይ ድማ ልቓሕ ካፒታል ብበዓል ዋናነት ንምሓዝ።

ሰ. ንፅንዓትን ምርምርን

ሸ/ ንስልጠና ህንፀት ዓቕሚ ወይ ድማ

ቀ) ኣብ'ዚ ንኡስ ዓንቀፅ ምስ ካብዚ ንላዕሊ ዝተዘርዘሩ ንዝተሓሓዝ ግልጋሎት ምኽሪ ዝተገበረ ወፃኢ'ዩ።

3. "ምትሕልላፍ ዕዳ" ማለት ፦ሓላፍነት ዕዳ ምኽፋል ካብ ሓደ ሰብ ፣ ትካል ወይ ሃገር ናብ ካልእ ምትሕልላፍ ኮይኑ ኣብ መንጎ ሰብ ዕዳ ወይ ገንዘብ ዝግበር ምትሕልላፍ ዝምልከት ክኸውን ይኽእል።

4. "ዋጋ ኣቕሑትን ግልጋሎትን" ማለት፦ ንኣቕርቦት ኣቕሓ፣ ግልጋሎት ንምርካብን ብመገልገልቲ ንምጥቃም ተጠቀምቲ ንቤት ዕዮታት ናይ'ቲ ክልል መንግስቲ ዝገብርዎ ክፍሊትን ኮይኑ መቕፃዕቲ ኣይሓውስን።


www.abyssinialaw.com

ለ/ መንገዶች እና ህንፃዎች ወይም ሌሎች ለመያዝ፣ለመስራት ወይም ለማዘጋጀት ወይም ለማሻሻል።

ሐ/ ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሣቀሱ ድርጅቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ መገልገያዎችን፣ ተሽከርካሪዎችን፣ አውሮፕላኖችን እና የመሳሰሉትን ለመያዝ ለመትከል ወይም ለመተካት፣

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ሀ-ሐ የተዘረዘሩትን ለመፈፀም ወይም የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ለመያዝ ለተደረገ ወይም ለሚደረግ ወጪ እንዲውል ለማናቸውም ሰው የቅድሚያ ክፍያ ዕርዳታ ወይም ሌላ ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ መስጠት፣

ረ/ የሕግ ሰውነት በተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ ካፒታል ወይም የብድር ካፒታል በባለቤትነት ለመያዝ፣

ሰ/ ለጥናትና ምርምር፣

ሸ/ ለአቅም ግንባታና ሥልጠና ወይም

ቀ) በዚህ ንኡስ አንቀፅ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ለተያያዘ የምክር አገልግሎት የተደረገ ወጪ ነው።

3 "ዕዳን ማስተላለፍ" ማለት፦ ዕዳን የመክፈል ኃላፊነትን ከአንድ ሰው፣ ድርጅት ወይም አገር ወደ ሌላ ማስተላለፍ ሲሆን በባለዕዳዎች ወይም በባለገንዘቦች መካከል የሚደረገውን ማስተላለፍ የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

4. "የዕቃና የአገልግሎት ዋጋ" ማለት፦ ለዕቃ አቅርቦት፣ አገልግሎት ለማግኘት እና በመገልገያዎች ለመጠቀም ተጠቃሚዎች ለክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚያደርጉት ክፍያ ሲሆን መቀጮ አይጨምርም።

www.abyssinialaw.com


5. "ፍዚካላዊ ማዕቀፍ" ማለት፡-

ሃፍቲ መንግስቲ እዚ ክልል ብትልሚ ማእኸላይ ዘመን ንክምራሕን ዝምደብ ዓመታዊ በጀት'ውን ምስ ምፍፃም ዕላማ ዝተረጋገፀ ኢኮኖሚ ዝተጠዓዓመ ክኸውን ንምግባር ንዝውሰን ናሕሲ በጀት መበገሲ ዝኾነ በቢዓመቱ ዝመዓራረ ናይ ሰለስተ ዓመት ግምት ኣታዊን ወፃእን መንግስቲ እንትኸውን ፣

ሀ/ ብመሰረት ፀኒዑ ብዘሎ መጠን ግብሪ መኽፈሊ ክእከብ'ዩ ተባሂሉ ዝተሓሰበ ኣታዊ ታክሲ መንግስቲ።

ለ/ ለውጢ ፖሊሲ ኣብ ዘይተገበረሉ ኹነታት ኣብ ዝሰርሕ ትልሚ ኣታዊ ታክሲ ካብ ዘይኮኑ ኣታዊታት መንግስቲ ( ካብ ልምዓታዊ ትካላት መንግስቲ ልምዓታዊ ትካላት ስራሕ ዝዘቐጠ ትርፊ፣ ካብ ክፍሊታት ፣ካብ ተጠቀምቲ ዝእከብ ዋጋ ወዘተ ክእከብ ተባሂሉ ዝሕሰብ ኣታዊ።

ሐ/ ዝለዓለ መጠን ግብሪ ብምውሳን ፣ ዝተፈለየ ስርዓት ግብሪ ብምዝርጋሕ፣ ወይ ድማ ብምኽንያት ኣተኣኻኽባ ግብሪ ትካላት ወይ ድማ መዋቕር ምምሕዳር መመሓየሺ ብምግባር ብተወሳኺ ክእከብ ዝኽእል ግምታዊ ታክሲ ኣታዊ።

መ/ ኣብ ልምዓታዊ ትካላት መንግስቲ ማዕቀፋዊ ፖሊሲ ፣ ኣብ ክፍለ ኢኮኖሚ መንግስቲ፣ ፖሊሲ ተመን ዋጋ ፣ ኣብ ልዕሊ ክፍሊታት ማሕበራዊ ግልጋሎት ለውጢ ብምግባሩ ምኽንያት ክርከብ'ዩ ተባሂሉ ዝሕሰብ ተወሳኺ ኣታዊ።

ረ/ ካብ ፍልፍላት ውሽጢ ሃገር ብልቓሕን ሓገዝን ክርከብ ይኽእል ተባሂሉ ዝሕሰብ ኣታዊ።

ሰ/ ወፃኢ ስሩዕን ካፒታልን ግምት

ሸ/ ካብ ፌዴራል መንግስቲ ክርከብ'ዩ ተባሂሉ ዝግመት ድጋፍ በጀት፣



5."የፊዚካል ማዕቀፍ"ማለት፡- የክልሉ መንግስት ሃብት በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንዲመራና የሚመደበውም ዓመታዊ በጀት የተረጋጋ ኢኮኖሚ ከማስፈፀም ዓላማ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ ለሚወሰን የበጀት ጣሪያ መነሻ የሆነ በየዓመቱ የሚስተካከል የሦስት ዓመት የመንግስት ገቢና ወጪ ግምት ሲሆን፣

ሀ/ ፀንቶ ባለው የግብር ማስከፈያ ምጣኔ መሠረት ይሰበሰባል ተብሎ የታሰበውን የመንግስት ታክስ ገቢ ።

ለ/ የፖሊሲ ለውጥ ባልተደረገበት ሁኔታ በሚሠራ የገቢ ዕቅድ ታክስ ካልሆኑ የመንግሥት ገቢዎች/ከመንግስት የልማት ሥራ ድርጅቶች የዘቀጠ ትርፍ፣ ከክፍያዎች፣ ከተጠቃሚዎች ከሚሰበሰብ ዋጋ ወ.ዘ.ተ/ ይሰበሰባል ተብሎ የታሰበውን ገቢ፣

ሐ/ ከፍ ያለ የግብር መጠን በመወሰን፣ የተለየ የግብር ሥርዓት በመዘርጋት ወይም በግብር አሰባሰብ ረገድ የተቋም ወይም የአስተዳደር መዋቅር ማሻሻያ በማድረግ በተጨማሪነት ሊሰበሰብ የሚችለውን የታክስ ገቢ ግምት፣

መ/ በመንግስት የልማት ሥራ ድርጅቶች የፖሊሲ ማዕቀፍ፣በመንግሥት ክፍለ ኢኮኖሚ የዋጋ ትመና ፖሊሲ፣ በማህበራዊ አገልግሎቶች ክፍያዎች ላይ ለውጥ በመደረጉ ምክንያት ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ተጨማሪ ገቢ፣

ረ/ ከአገር ውስጥ ምንጮች በብድር እና በእርዳታ ሊገኝ ይችላል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ፣

ሰ/ የመደበኛ እና የካፒታል ወጪ ግምት።

ሸ/ ከፌዴራል መንግስት ይገኛል ተብሎ የሚገመተውን የበጀት ድጋፍ

www.abyssinialaw.com



ቀ/ ናይ'ዚ ክልል ጉድለት በጀትን ግምት ኣሸፋፍና ጉድለት በጀትን

6. " ዝመሓላለፍ ናይ ገንዘብ ሰነድ"ማለት፡- ብዘይ ፊርማ ወይ ፊርማ ብምግባር ካብ ሓደ ሰብ ናብ'ቲ ኻልእ ብምትሕልላፉ ምኽንያት ንዝመሓላለፈሉ ሰብ መሰል በዓል ዋናነት ዘርክብ ሰነድ ገንዘብ'ዩ።

7. "ትሕጃ ውሕስና" ማለት ፦

1. ሰነድ ሓዋላ ኾይኑ፡-

ሀ. ንናይ'ቲ ክልል ቢሮ ትልምን ፋይናንስን ዝኽፈልን ፣

ለ. ብዝተፈለጠ ትካል ገንዘብ ዝተረጋገፀ ወይ ድማ ብኽሙ ዝወፀ

2. ብመንግስቲ ውሕስና ዝተውሃበ ቦንድ ወይ ድማ፣

3. ኣብ ናይ'ቲ ክልል ቤት ዕዮ መንግስቲ ተቐባልነት ክህልዎ ዝኽእልን በቲ ቢሮ ዝፀደቐ ካልእ ተመሳሳሊ ውሕስና'ዩ።

8. "ኣዋጅ" ማለት፦ ኣመሓዳድራ መንግስታዊ ፋይናንስ ብ/ክ/መ/ትግራይ ኣዋጅ ቁፅሪ 173/2002 እዩ።

9. "መዝገብ" ማለት፡- ብሰነድ ወይ ብሜላ ኤሌክትሮኒክስ ኣቢሉ ዝተሓዝ መረዳእታ'ዩ ፡፡

10. ብናይ'ዚ ክልል ምምሕዳር ፋይናንስ ኣዋጅ ትርጉም ዝተውሃቦም ኣብ ውሽጢ'ዚ ደንቢ'ዚ ኣብ ጥቕሚ ዝወዓሉ ቃላትን ሓረጋትን በቲ ኣዋጅ ዝተውሃቦም ትርጉም ይሕዙ።

11. "ቢሮ" ማለት፦ቢሮ ትልምን ፋይናንስን እዩ።

12. " ክልል " ማለት ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ'ዩ።

ቀ/ የክልሉን የበጀት ጉድለት እና የበጀት ጉድለቱ ኣሸፋፈን ግምትን

6. "የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ" ማለት፡- በፊርማ ወይም ያለፊርማ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ በመተላለፉ ምክንያት ለተላለፈለት ሰው የባለቤትነት መብት የሚያስገኝ የገንዘብ ሰነድ ነው።

7. "የዋስትና መያዣ" ማለት

1. የሓዋላ ሰነድ ሆኖ፡-

ሀ. ለክልሉ ፕላንና ፋይናንስ ቢሮ የሚከፈል፣ እና

ለ. በታወቀ የገንዘብ ተቋም የተረጋገጠ ወይም በታወቀው የገንዘብ ተቋም በራሱ ስም የወጣ፣

2. በመንግሥት ዋሰትና የተሰጠበት ቦንድ ወይም

3. በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል እና በቢሮው የፀደቀ ሌላ ተመሣሣይ ዋሰትና ነው።

8. "ኣዋጅ" ማለት፡- የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ ኣስተዳደር ኣዋጅ ቁጥር 173/2002 ነው።

9. "መዝገብ"ማለት፡- በሰነድ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ኣማካኝነት የሚያዝ መረጃ ነው፡፡

10. በክልሉ የፋይናንስ ኣስተዳደር ኣዋጅ ትርጉም የተሰጣቸው በዚህ ደንብ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በኣዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

11. "ቢሮ ማለት፦ቢሮ ፕላንና ፋይናንስነው።

12. "ክልል" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።

www.abyssinialaw.com

## ክፍሊ ክልተ

## በጀት

### 3. መትከል

1. በጀት መንግስቲ ኣብ ትልሚ ዝተመስረተ ክኸውን ኣለዎ።
2. በጀት መንግስቲ ዝዳለዉ ፊዚካላዊ ማእቀፍ መሰረት ብምግባር ይኸውን
3. ትልሚ ልምዓት ማእኸላይ ዘመን ብላዕለዎት ሓለፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ክዳለዉ ይግባእ፣
4. ግምት በጀት ኣታውን ወፃእን ዝዳለዉ ንቐፃሊ በጀት ዓመት ክኸውን ኣለዎ፣
5. ዝኾነ ናይ ወፃኢ ካፒታል ኣብ ውሽጢ ፊሲካል ማዕቀፍ ንሕድ ሕድ ክፍለ ኢኮኖሚ ልዕሊ ዝተቐመጠ ናሕሲ ክኸውን ኣይኽእልን፣
6. ኣብ ውሽጢ ካፒታል በጀት ንክፍልታት ኢኮኖሚ ዝወሃብ ቐዳምነት ዝውሰን ኣብ ፊዚካል ማዕቀፍ ዝተቐመጠ ቅደም ስዓብ መሰረት ብምግባር ይኸውን፣
7. ብኣታዊ ምጥቃም ንክኽእል ዝተፈቕደሉ መንግስታዊ ቤት ዕዮ እንትህሉ ከምዚ ዓይነት ኣታዊ ነቲ ቤት ዕዮ ብዝተፈቕደ ኣታዊ ከምኡ'ውን ድምር ወፃኢ በጀት ውሽጢ ክጠቓለል ይግበኦ፡፡ ዝተፃረየ ሒሳብ ክርኢ ኣይፍቀድን።

### 4. ኣቀራርባን ኣደላልዋን በጀት

1. ግምታዊ በጀት ዝዳለዉ ብናይቲ ክልል ስራሕ ፈፃሚ ብዝፍቀድ ፊዚካላዊ ማዕቀፍ መበገሲ እቲ ቢሮ በቢ ዓመቱ ደብዳቤ ፃውዒት በጀት ዘፍልጦ ናሕሲን ስርዓት ኣቀራርባ በጀትን መሰረት ብምግባር ይኸውን።
2. ስሩዕ ወፃኢ ግምታዊ በጀት ናይ'ቲ ዘመን ናይ መጀመሪያ ፍርቂ ዓመት በጀት ግዚያዊ ፀብፃብን ዝሓለፈ ዓመት ኣፈፃፅማ በጀት ዘጠቓልል ክኸውን ይግባእ።

## ክፍል ሁለት-

## በጀት

### 3. መርህ

1. የመንግስት በጀት በዕቅድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፣
2. የመንግስት በጀት የሚዘጋጀው የፊሲካል ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ ይሆናል፣
3. የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ በመንግስት መስሪያቤቶች የበላይ ሃላፊዎች መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
4. የገቢ እና የወጪ በጀት ግምት የሚዘጋጀው ለተከታዩ የበጀት ዓመት መሆን አለበት፣
5. ማናቸውም የካፒታል ወጪ በፊሲካል ማዕቀፍ ውስጥ ለየክፍለ - ኢኮኖሚው ከተመለከተው ጣሪያ በላይ ሊሆን አይችልም፣
6. በካፒታል በጀት ውስጥ ለክፍለ ኢኮኖሚ ክፍሎች የሚሰጠው ቀዳሚነት የሚወሰነው በፊሲካል ማዕቀፍ የተመለከተውን ቀደምትነት መሰረት በማድረግ ይሆናል።
7. በገቢው መጠቀም እንዲችል የተፈቀደለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢኖር፣ የዚህ ዓይነቱ ገቢ ለመሥሪያ ቤቱ በተፈቀደው ገቢ እንዲሁም የወጪ በጀት ድምር ውስጥ መጠቃለል ይኖርበታል፣ የተጣራ ሂሣብን ማሳየት አይፈቀድም።

### 4. የበጀት ዝግጅት እና አቀራረብ

1. የበጀት ግምት የሚዘጋጀው በክልሉ ስራ አስፈፃሚ በሚፈቀደው የፊሲካል ማዕቀፍ መነሻ ቢሮው በየዓመታዊው የበጀት ጥሪ ደብዳቤ የሚያስታውቀውን ጣሪያ እና የበጀት አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ይሆናል።
2. የመደበኛ ወጪ የበጀት ግምት የዘመኑን የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት በጀት ጊዜያዊ ሪፖርት እና ያለፈውን ዓመት የበጀት አፈጻጸም የሚያጠቃልል ሊሆን ይገባል።

3. ስሩዕን ካፒታልን ወፃኢ በጀት ግምታት ብላዕለዎት ሓለፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ክፍረሙ ኣለዎም።
4. ታክስ ተንከፍ ካብ ዝኾኑ ፍልፍላት ዝእከብ ኣታዊ ግምት በጀት በቲ ቢሮ ዝዳሎ ይኸውን፣
5. ታክሲ ካብዘይኮኑ ፍልፍላት ኣታዊ በጀት ሓላፍነት ብዝተውሃቦ ቤት ዕዮ መንግስቲ ላዕለዋይ ሓላፊ ተዳልዩ ናብ'ቲ ቢሮ ክቐርብ ኣለዎ።
6. ስሩዕን ካፒታልን በጀት ግምት ገምጋም፣ ኣድላይ ኣብ ዝኾነሉ ግዜ'ውን ከምብሓዱሽ ክረአ ንምግባርን ንመጠቓለሊ ስራሕቲን ናብቲ ቢሮ ክቐርብ ኣለዎ።
7. ግምት በጀት ካብ ውሽጢ ሃገር ዝርከብ ልቓሕን ካብ ፌደራል መንግስቲ ዝርከብ ድጋፍ በጀትን ከምኡ'ውን ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ኣብ'ቲ ዝስዕብ በጀት ዓመት ብጥረ ገንዘብን ብዓይነትን ክረክብ'ዩ ኢሉ ዝህልዎ ግምት ሓገዝ፣ ብዓይነት ዝርከብ ሓገዝን ብገንዘብ የውፅእ'ዩ ተባሂሉ ዝግምትን ዋጋ ዝተማልአ ዝርዝር ዝሕዝ ክኸውን ኣለዎ፡፡

## 5. ምፅዳቕ በጀት ግምት

1. ናይ'ቲ በጀት ግምት ምስ ተገምገመን ኣድላይ ዘበለ ምዕራይ ምስ ተገበረ ከምኡ'ውን ምስ ላዕለዎት ሓላፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ዝግበር ዘተ ድሕሪ ምውድኡ ቢሮ ሓላፊ ዝተጠቓለለ ስሩዕን ካፒታልን በጀታዊ ግምት ተራእዩ ንኽድገፍ ቅድሚ ናብ በጀትን ኦዲትን ቀዋሚ ኮሚቴ ምቕራቡ ናብቲ ክልል ፈፃሚ ስራሕ የቕርብ።

3. የመደበኛ እና የካፒታል ወጪ በጀት ግምቶች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች መፈረም አለባቸው።
4. ታክስ ነክ ከሆኑ የገቢ ምንጮች የሚሰበሰበው የገቢ በጀት ግምት በቢሮው የሚዘጋጅ ይሆናል።
5. ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች የገቢ በጀት ግምት ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ተዘጋጅቶ ለቢሮው መቅረብ አለበት።
6. የካፒታልና የመደበኛ ወጪ የበጀት ግምት ለግምገማ፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም እንደገና እንዲታይ ለማድረግ እና ለማጠቃለያ ሥራዎች ለቢሮው መቅረብ አለበት።
7. የበጀት ግምት ከአገር ውስጥ የሚገኘውን ብድርና ከፌደራል መንግስት የሚገኘውን የበጀት ድጋፍ እንዲሁም ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተከታዩ የበጀት ዓመት በጥሬ ገንዘብና በዓይነት አገኛለሁ ብሎ የሚጠብቀውን እርዳታ ግምት፣ በዓይነት የሚገኘውን እርዳታ ዓይነትና፣ በገንዘብ ያወጣል ተብሎ የሚገመተውን ዋጋ የተሟላ ዝርዝር የያዘ መሆን አለበት።

## 5. የበጀት ግምትን ማጽደቅ

1. የበጀቱ ግምት ከተገመገመ እና አስፈላጊ የሆነው ሁሉ ማጣራት ከተከናወነ እንዲሁም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር የሚደረገው ውይይት ከተጠናቀቀ በኋላ የቢሮ ሓላፊው የተጠቃለለው የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ግምት ታይቶ እንዲደገፍ ለበጀትና ኦዲት ቋሚ ኮሚቴ ከመቅረቡ በፊት ለክልሉ ስራ አስፈፃሚ ያቀርባል።

www.abyssinialaw.com


2. ብናይቲ ክልል ፈፃሚ ስራሕ ዝተደገፈ በጀታዊ ግምት ናብ ክልል ቤት ምኽሪ ይቐርብ።
3. ሓላፊ ናይ'ቲ ቢሮ ብናይ'ቲ ክልል ቤት ምኽሪ ዝፀደቐ በጀት ላዕለዎት ሓለፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ፅዮ ክፈልጡ ይገብር።

## 6. ግዜ ሰደቓ በጀት

እቲ ቢሮ ግዜ ሰሌዳ በጀት ዝውስን መምርሒ የውፅእ።

## 7. ፍሉይ ስልጣን

ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ፅዮ በዚ ደንቢ ዓንቀፅ 6 መሰረት እቲ ቢሮ ብዝውስኖ ግዜ ሰደቓ ግምት በጀት እንተዘይ ኣቕሪቡ እቲ ሓላፊ ቢሮ ናይ ባዕሉ ፍሉይ ስልጣን ተጠቒሙ ኣብ ውሽጢ ግምታዊ በጀት እንታይ ክሕወስ ከምዘለዎ ይውስን

## 8. ዝውውር በጀት

1. ሓላፊ ቢሮ ብዝፀደቐ መንግስታዊ ቤት ፅዮ ለውጢ ኣወዳድባ ምኽንያት ንሽቶ ዕላማታት መንግስቲ ኣድላይ ኾይኑ እንተረኺብዎ ካብ ስሩዕ ናብ ካፒታል በጀት ዝውውር ንኽግበር ክፈቅድ ይኽእል።
2. ካብ ካልኦት ስሩዕ ወፃኢታት በጀት ናብ መሃያ፣ ናብ ንሰራሕተኛታት ዝኽፈል ናይ ሓፂር ግዜ ፣ ጉልበት ወይ ዋጋ ግልጋሎት ወይ ዝውውር ኣበል በጀት ክግበር ዝኽእል ንቢሮ ትልምን ፋይናንስን ብሂራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ሓላፊ ቀሪቡ እንትፍቀድ ይኸውን።

2. በክልሉ ስራ አስፈፃሚ የተደገፈው የበጀት ግምት ለክልሉ ምክር ቤት ይቀርባል።
3. የቢሮ ሓላፊው በክልሉ ምክር ቤት የፀደቀውን በጀት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች እንዲያውቁ ያደርጋል።

## 6. የበጀት የጊዜ ሰሌዳ

ቢሮው የበጀት የጊዜ ሰሌዳን የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

## 7. ልዩ ሥልጣን

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሠረት በሚወሰነው የጊዜ ሠሌዳ የበጀቱን ግምት ካላቀረበ የቢሮ ሓላፊው የራሱን ልዩ ሥልጣን በመጠቀም በበጀቱ ግምት ውስጥ ምን መካተት እንደሚገባው ይወስናል።

## 8. የበጀት ዝውውር

1. የቢሮ ሓላፊው በፀደቀ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት ለመንግሥት ዓላማዎች ግብ መድረስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከመደበኛ ወደ ካፒታል በጀት ዝውውር እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።
2. ከሌሎች መደበኛ ወጪዎች በጀት ወደ ደመወዝ፣ ለሠራተኛ ወደሚከፈል የአጭር ጊዜ የጉልበት ወይም የአገልግሎት ዋጋ ወይም ወደ አበል የበጀት ዝውውር ሊደረግ የሚችለው ለትግራይ ቢሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፕላንና ፋይናንስ ቢሮ ሐላፊ ቀርቦ ሲፈቀድ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com



3. ሓደ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ዝተፈቕደሉ በጀት ዘይጥቀመሉ ኾይኑ ኣብ ዝተረኽበሉ እዋን ናብ ካልእ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ምዝውዋር ንኽከኣል እቲ ቢሮ ኣፈፃፅማ በጀት ንምክትታል ዘኽእል ስርዓት ይዝርግሕ። እቲ ዝውውር ዝፍፀመሉ ኹነታት ዝውስን መምርሒ የውፅእ።

4. ናይ'ቲ ሓላፊ ቢሮ በቲ ኣዋጅ ዓንቀፅ 24 መሰረት ኣብ ውሽጢ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ብዛዕባ ዝግበር ዝውውር በጀት እቲ ዝተዋህቦ በጀት ምዝውዋር ስልጣን ብምልኡ ወይ ብኽፋል ንላዕለዎት ሓለፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ክህብ ይኽእል፡፡ ዝርዝር ኣፈፃፅምኡ ብመምርሒ ይውሰን፡፡

## 9. ቑፅፅር በጀት

1. ላዕለዎት ሓለፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ካብ'ዚ ቢሮ ብዝመሓላለፍ መምርሒ መሰረት ንሕድሕድ በጀት ርእሲ፣ ንኡስ ርእስን ሕድሕድ ካፒታል ፕሮጀክት ዝተፈቐዶ ዝውውርን ድልድልን ዘርኢ መዝገብ በጀት ክሕዙ ኣለዎም ።

2. ላዕለዎት ሓለፍቲ መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ በቲ ቢሮ ብዝመሓላለፍ መምርሒ መሰረት መንግስቲ በጀት ብዝተማእኸለ መልክዑ ንምቁፅፃር ዘኽእሎ መረዳእታ ክህቡ ኣለዎም።

## 10. ተወሳኺ በጀት

1. ሕቶ ተወሳኺ በጀት ምቕራብ ኣድላይ ኾይኑ እንተርከብ እቲ ሕቶ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ተዳልዩ ንሓላፊ ቢሮ ይቐርብ።

3. አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደለትን በጀት የማይጠቀምበት ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ማዘዋወር እንዲቻል ቢሮው የበጀት አፈፃፀምን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል ፣ ዝውውሩ የሚፈፀምበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

4. የቢሮ ኋላፊው በኣዋጅ አንቀፅ 24 መሰረት መንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ስለሚደረግ የበጀት ዝውውር የተሰጠውን በጀት የማዘዋወር ስልጣን በሙሉ ወይም በከፊል ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 9. የበጀት ቁጥጥር

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊ ዎች ከቢሮው በሚተላለፈው መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ የበጀት ርዕስ፣ ንኡስ ርዕስ እና ለእያንዳንዱ የካፒታል ፕሮጀክትየተፈቀደውን ዝውውር እና ድልድል የሚያሳይ የበጀት መዝገብ መያዝ አለባቸው

2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በቢሮው በሚተላለፍ መመሪያ መሠረት መንግሥት በበጀት ላይ በማዕከላዊነት ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችለውን መረጃ መስጠት አለባቸው።

## 10. ተጨማሪ በጀት

1. የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥያቄው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተዘጋጅቶ ለቢሮ ኃላፊው ይቀርባል።

www.abyssinialaw.com



2. ቢሮ ሓላፊ ኣብ ኣዋጅ ብዝተቐመጠ በጀት ናይ ምዕዳኞን ምፍላጥን ስርዓት ተኸቲሉ ተወሳኺ በጀት ንክፀድቕን ኣብ ስራሕ ክውዕልን ይገብር።

11. **ኣፈፃፅማ ዝውውር በጀት**

ዝኾነ ዝውውር በጀት ዝሓትት ወይ ድማ ብመሰረት ዝተውሃቦ ውክልና ዝፍፅም መንግስታዊ ቤት ፅዮ እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ቅጥዒታት መሕተትን መፍቀድን በጀት ብእኹል ቅዳሕ ክመልእ ኣለዎ።

**ክፍሊ-ሰለስተ**

**ክፍሊት መንግስታዊ ገንዘብ**

12. **ክፍሊትን ወፃኢን**

ክፍሊት መንግስታዊ ገንዝብ ክፍፀም ወይ ወፃኢ ክግበር ዝኽእል ዝተፈቐደ በጀት እንትህሉ ጥራሕ'ዩ።

13. **ወፃኢ መአዘዚ መንግስታዊ ገንዘብ**

እቲ ግቡእ መአዘዚ ከይተማልአ ዝኾነ ይኹን ክፍሊት መንግስታዊ ገንዘብ ክፍፀም

ወይ ወፃኢ ክግበር ኣይከኣልን።

ስለ ዝኾነ ድማ መንግስታዊ ኣብያተ ፅዮ ንዝገብርዎ ኩሉ ወፃኢ ካብ'ቲ ቢሮ ብዝወፅእ መምርሒ መሰረት መአዘዚ ክመልኡ ኣለዎም።



2. የቢሮ ኃላፊው በኣዋጁ የተቀመጠውን የበጀት ማስፅደቅና ማሳወቅ ሥርዓት ተከትሎ ተጨማሪ በጀትን ያስፀድቃል ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

11. **የበጀት ዝውውር አፈፃፀም**

ማናቸውም የበጀት ዝውውር የሚጠይቅ ወይም በተሰጠው ውክልና መሠረት ዝውውር የሚፈፅም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የበጀት መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጾችን በበቂ ቅጂ መሙላት አለበት።

**ክፍል ሦስት**

**የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ**

12. **ክፍያ እና ወጪ**

የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው።

13. **የመንግስት ገንዘብ ወጪ ማዘዣ**

ተገቢው ማዘዣ ሳይሟላ ማናቸውም የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ አይችልም። ስለሆነም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚያደርጉት ወጪ ሁሉ ከቢሮው በሚወጣው መመሪያ መሠረት ማዘዣ መሙላት አለባቸው።

www.abyssinialaw.com



## 14. ውክልና ብዛዕባ ዝተውሃቦም ሰባት ዝርዝር

1. ላዕለዋይ ሓላፊ ሕድሕድ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ኣብ'ዚ ደንቢ ዝተቐመጡ ሰነዳት ንኽፍርሙ ውክልና ዝተውሃቦም ሓለፍትን ሰራሕተኛታትን ሽም ዝርዝር ከዳሉን ክሕዝን ኣለዎ።
2. ከምዚ ዝበለ ሽም ዝርዝር ንቤት ዕዮ ሒሳብ ሓላፊ ፣ ንውሽጢ ኦዲት ሓላፊን ነቲ ቢሮን ክመሓላለፍ ኣለዎ።

## 15. ምምሕዳር ጥረ ገንዘብ

1. ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ ፕሮግራም ስርሖም ንኽፍፅሙ ዝተመደበሎም በጀት ወፃኢ ኣብ ስራሕ ንከውዕልዎ ዝህልዎም ድልየት ጥረ ገንዘብን ፍሰት ጥረ ገንዘብን መንግስታዊ ግምጃ ቤት መሰረት ብምግባር ሚዛን ሒሳብ ብትሑት መጠን ንኽፀንሕ ምግባር ብዘኽእል ኩነታት ክምራሕ ይግበኦ፣
2. ኣብ'ዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተመልከተ ኣብ ስራሕ ምውዓል ንኽከኣል ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ ኣብ ዜሮ ሚዛን ዝተመስረተ ስርዓት ምምሕዳር ጥረ ገንዘብ ንክኽተሉ ይገብር፣
3. ላዕለዎት ሓለፍቲ ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ ኣብ ውሽጢ 3 ወርሒ ዝህልዎም ትልሚ ድልየት ጥረ ገንዘብ በብወርሑ ብምክፍፋል ነቲ ቢሮ ክቕርቡ ኣለዎም፣
4. ካብ'ዚ ንላዕሊ ኣብ ንኡስ ዓንቀፅ 3 ኣብ ዝተገለፀን እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ ትልሚ ጥረ ገንዘብ

## 14. ውክልና ስለተሰጣቸው ሰዎች ዝርዝር

1. እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ሰነዶች እንዲፈርሙ ውክልና የተሰጣቸውን ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስም ዝርዝር ማዘጋጀትና መያዝ አለበት።
2. እንዲህ ያለው የስም ዝርዝር ለመሥሪያ ቤቱ ሂሣብ ኃላፊ፣ ለውስጥ ኦዲት ኃላፊ፣ እና ለቢሮው መተላለፍ አለበት።

## 15. የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር

1. የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሥራ ፕሮግራ ማቸውን ለማስፈፀም የተመደበላቸው የወጪ በጀት ሥራላይ ለማዋል የሚኖራቸውን የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት እና የመንግስት ግምጃ ቤትን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መሰረት በማድረግ የሂሳብ ሚዛን በዝቅተኛ መጠን እንዲቆይ ማድረግ በሚያስችል ሁኔታ መመራት ይኖርበታል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ሥራ ላይ ማዋል እንዲቻል የመንግስት መስሪያ ቤቶች በዜሮ ሚዛን ላይ የተመሰረተ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት እንዲከተሉ ያደርጋል፣
3. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በሦስት ወር ውስጥ የሚኖራቸውን የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ዕቅድ በየወሩ በመከፋፈል ለቢሮው ማቅረብ አለባቸው፣
4. ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀፅ 3 በተገለፀው እና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የመንግስት መስሪያቤቶች የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ

እንተዘይኣቕሪቦም እቲ ቢሮ ካብ ዘለዎ መረዳእታ ተመስሪቱ መጠኑ ይውስን፣

5. ትልሚ ጥረ ገንዘብ ነናይ ወርሑ መጠን ወፃኢ ከምኡ'ውን እቲ ገንዘብ ዝድለየሉ ግዜ ዘርኢ ክኸውን ኣለዎ፣

6. ካብ'ዚ ንላዕሊ ኣብ ንኡስ ዓንቀፅ 5 ዝተጠቐሰ ከምዘሎ ኾይኑ ኣታዊ ኣከብቲ መንግስቲ ነናይ ወርሑ ትልሚ ኣታዊን ኣፈፃፅማ ኣታዊ ሕሉፍ ወርሒን ነቲ ቢሮ ከቕርቡ ኣለዎም፡፡

## 16. ምኽፋልን ወፃኢ ምግባርን ገንዘብ መንግስቲ

1. ክፍሊት ገንዘብ መንግስቲ ዝፍፀም ወይ ወፃኢ ዝግበር እቲ ገንዘብ ክፍሊት ናብ ዝፍፀመሉ ቤት ፅዮ መንግስቲ ወይ ወፃኢ ናብ ዝግበረሉ በዓል መሰል ባንኪ ሒሳብ ብምምሕልላፍ ይኸውን፣

2. ኣብ'ዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተቐመጠ እንተሃለወ'ውን ወፃኢ ብቼክ፣ ብሌተር ኦፍ ክረዲት ወይ ብጥረ ገንዘብ ዝፍፀመሉ ኹነታት እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ ይውሰን፣

3. ክፍሊት ገንዘብ መንግስቲ ዝፍፀም ኣብያተ ፅዮ መንግስቲ ብዘቕረብዎ ትልሚ ጥረ ገንዘብ መበገሲ ብምግባር ቢሮ ብዝውስኖ ናሕሲ መሰረት ይኸውን፡፡

## 17. ድሕንነት ኣብ ኢድ ተሓዝቲ ገንዘብ ዝቕመጥ ገንዘብ መንግስቲ

ሓላፊ ናይ'ቲ ቢሮ ኣብ ኢድ ገንዘብ ተሓዝቲ ዝቕመጥ ገንዘብ መንግስቲ ብዝተፈላለየ

ካላቀረቡ ቢሮው ባለው መረጃ ላይ በመመሥረት መጠኑን ይወሰናል፣

5. የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ የየወሩን የወጪ መጠን እንዲሁም ገንዘቡ የሚፈለግበትን ጊዜ የሚያሳይ መሆን አለበት፣

6. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ገቢ ሰብሳቢ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የየወሩን የገቢ ዕቅድና ያለፈውን ወር ገቢ አፈፃፀም ለቢሮው ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 16. የመንግስት ገንዘብ ስለመክፈልና ወጪ ስለማድረግ

1. የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ የሚፈፀመው ወይም ወጪ የሚደረገው የገንዘቡ ክፍያ ወደ ሚፈፀምለት የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም ወጪ ወደሚደረግለት ባለመብት የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ወጪ በቼክ፣ በሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚፈፀምበት ሁኔታ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

3. የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ የሚፈፀመው የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሚያቀርቡት የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ መነሻ ቢሮው በሚወስነው ጣሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

## 17. በገንዘብ ያዦች እጅ ስለሚቀመጥ የመንግስት ገንዘብ ደህንነት

የቢሮ ኃላፊው በገንዘብ ያዦች እጅ የሚቀመጠው የመንግስት ገንዘብ በተለያየ

ምኽንያት ኣብ ዝጠፍአሉ ግዜ ነቲ ገንዘብ ንምትካእ ዝኽእል ውሕስና መድሕን ዝአተወሉ ስርዓት የመዓራሪ፡፡

## ክፍሊ ኣርባዕተ
## ዋጋ ግልጋሎትን ኣቕሑትን

18. መትከል

መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ዋጋ ኣቕሑትን ግልጋሎትን ኣብ ዝውስንሉ እዋን ነዞም ዝስዕቡ መትከላት ኣብ ግምት ውሽጢ ክአትዉ ይግበኦም።

1. ንግብሪ ሽፋሊ ሕብረተሰብ ፍትሓዊ ንምኳን ኣብያተዕዮ መንግስቲ ንዘቕርብዎ ግልጋሎት ዘድሊ ዕዕንቶ ወፃኢ ብሓፈሽኡ ኣብ ልዕሊ ግብሪ ሽፋሊ ሕብረተሰብ ካብ ዝዓርፍ ኣብ ልዕሊ ናይ'ቲ ግልጋሎት ተጠቃሚ ኣብ ዝኾነ ክፋል ሕብረተሰብ ዝዓርፈሉ መንገዲ ምድላይን ወይ ድማ፡-
2. ኣቕርቦት ኣቕሑትን ግልጋሎትን ዕዳጋ ዝመርሕ ስርዓት ንክኽተል ብምግባር ብቕዓት አጠቓቕማ ሃፍቲ ምዕባይ።

19. ብምፅናዕ ኣቕርቦት ኣቕሑትን ግልጋሎትን

መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ዝተመስረትሉ ሕጊ መሰረት ብምግባር ካብ ዝሰርሕዎም ተግባራት ውሽጢ ካብ ተጠቀምቲ ዋጋ ኣቕሑትን ግልጋሎትን ንምሕታት ዝከኣሎም ንምፍላይ ኣብ ልዕሊ ምንቅስቓሶም ፅንዓት ከካይዱ አለዎም።

ምክንያት በሚጠፋበት ግዜ ገንዘቡን ለመተካት የሚያስችል የመድን ዋስትና የሚገባበትን ስርዓት ያመቻቻል፡፡

## ክፍል አራት
## ዕቃና የአገልግሎት ዋጋ

18. መርህ

የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የዕቃና የአገልግሎት ዋጋ ልክ በሚወስኑበት ጊዜ የሚከተሉትን መርሆዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፣

1. ለግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ ፍትሀዊ ለመሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት የሚያስፈልገው የወጪ ጫና በአጠቃላይ በግብር ከፋይ ኅብረተሰብ ላይ ከሚያርፍ የአገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ የሚያርፍበትን መንገድ መፈለግ እና/ወይም
2. የዕቃዎችና የአገልግሎቶች አቅርቦት የገበያ መር ሥርዓት እንዲከተል በማድረግ የሃብት አጠቃቀምን ብቃት ማሳደግ።

19. የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦትን ስለማጥናት

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ህግ መሠረት በማድረግ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ ከተጠቃሚዎች የዕቃና አገልግሎት ዋጋ ለመጠየቅ የሚቻልባቸውን ለመለየት በእንቅስቃሴዎቻቸው ላይ ጥናት ማካሄድ አለባቸው።

www.abyssinialaw.com



20. ዓቐን ክፍሊታት ኣቑሑትን ግልጋሎትን መወሰኒ መመዘኒታት

መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ዓቐን ዋጋ ኣቕሑትን ግልጋሎትን ኣብ ዝውስንሉ እዋን ዝስዕቡ ኣብ ግምት ውሽጢ ከእትው አለዎም።

1. ወፃኢ ክፍሊት ኣቑሑትን ግልጋሎትን፣
2. ዋጋ ኣቑሑትን ግልጋሎትን ኣታዊ ብምፍጣር መዳይ ዘለዎ ዓቕሚን ከምኡ' ውን ዋጋ ኣብ ዝኸፈለሉ ምንቅስቓስን ኣብ ልዕሊ ካልኦት መንግስታዊ ተግባራት ዝህልዎ ውፅኢትን
3. ተጠቀመቲ ብኣንፃር ዕሬትን ዋጋን ኣቕሓ ወይ ድማ ግልጋሎት ንምኽፋል ዘለዎም ፍቓደኛነትን ዓቕምን፣
4. ተጠቀምቲ ዕሬት፣ ዋጋን ግልጋሎት ኣቑሕትን ኣፅጋቢ ብዛዕባ ምኳኑ ዘለዎም ሪኢቶ ።

21. ምፅዳቕ

1. ሳዕለዎት ሓለፍቲ መንግስቲዊ ኣብያተ ዕዮ ሓደሽቲ ዋጋታትን ከምኡ'ውን ኣብ ነባር ክፍሊታት ዝግበር ለውጢ ብዝምልከት ዘለዎም ናይ ውሳኔ ሓሳብ ብሓላፊ ቢሮ ኣቢሎም ንፈፃሚ ስራሕ እቲ ክልል ኣቕሪቦም ከፅድቑ ይግበኦም።
2. ኣብ'ዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተሓገገ እንተሃለወ'ውን መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ንሕብረተሰብ ዘቕርብዎ ኣቕሓን ዝህብዎ ግልጋሎትን ብስሩዕነት ዝትግበር እንተዘይኮይኑ ወይ ድማ ንኣቕሓን ንግልጋሎትን ዝሓቶ ነፀላ ዋጋ ካብ ብር 50



20. የዕቃና የአገልግሎት ክፍያዎችን ልክ የመወሰኛ መመዘኛዎች

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የዕቃና የአገልግሎት ዋጋ ልክ በሚወስኑበት ጊዜ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

1. የዕቃና ክፍያ የአገልግሎት ወጪ
2. የዕቃና የአገልግሎት ዋጋ ገቢ በማመንጨት ረገድ ያለውን አቅም እንዲሁም ዋጋ በሚከፈልበት እንቅስቃሴ እና በሌሎችም የመንግሥት ተግባራት ላይ የሚኖረውን ውጤት፣
3. ተጠቃሚዎች ከዕቃው ወይም ከአገልግሎቱ ጥራት እና ከዋጋው አንጻር ለመክፈል ያላቸውን ፈቃደኝነት እና አቅም፣
4. ተጠቃሚዎች የዕቃዎችና የአገልግሎች፣ ጥራት እና ዋጋ አጥጋቢ ስለመሆኑ ያላቸውን አስተያየት

21. ማፅደቅ

1. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋዎችን እንዲሁም በነባር ክፍያዎ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በቢሮ ኃላፊው በኩል ለክልሉ ስራ አስፈፃሚ አቅርበው ማፅደቅ ይኖርባቸዋል
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቶች ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡት ዕቃና የሚሰጡት ኣገልግሎት በመደበኝነት የሚከናወን ካልሆነ ወይም ለዕቃው እና ለኣገልግሎቱ የሚጠየቀው የተናጠል ዋጋ ከብር 50 (ሓምሳ ብር)

www.abyssinialaw.com



(ሓምሳ ብር) ዘይበልፅ እንተኾይኑ ዓቐን እቲ ክፍሊት ብሓላፊ ቢሮ ክፀድቕ ይኽእል።

## 22. ምፍላጥ ፣

መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ብዝፀድቁ ሓደሽቲ ዋጋታት ኣቕሑትን ግልጋሎትን ከምኡ'ውን ኣብ ልዕሊ እቶም ዝፀንሑ ዋጋታት ዝትግበሩን ዝፀድቑን ምምሕያሻትን ዝርዝር ዝፀንዓሉ መዓልቲ'ውን ንሕ/ሰብ ክፍልጡ ኣለዎም።

## 23. ምምርማር

መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ ካብ'ቲ ቢሮ ብዝወፅእ መምርሒ ብዝውሰን ግዜ ኣፈላላይ መጠን ዋጋ ኣቕሑትን ግልጋሎትን ተመጣጣኒ ብዛዕባ ምዃኑ ገምጋም ክካይዱ ኣለዎም።

# ክፍሊ ሓሙሽተ

## ምእካብን ኣታዊ ምግባርን ገንዘብ መንግስቲ

## 24. ምእካብ መንግስታዊ ገንዘብ

መንግስታዊ ገንዘብ ንምእካብ ብሕጊ ግቡእ ዘለዎ ላዕለዋይ ሓላፊ ሕድሕድ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ገንዘብ ኣተኣኻኽባ ተግባር ዝተማልአን ብቕዓትዘለዎ ስርዓት ውሽጢ ቑፅፅር ምህላውን ገንዘብ መንግስቲ ብዝግባእ ዝተአከበ ምዃኑን ከረጋግፅ ኣለዎ።

## 25. ምቕባል ገንዘብ መንግስቲ

1. ብሽም ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝእከብ ዝኾነ ገንዘብ ተኸታታሊ ቁፅሪ ዘለዎ በቲ ቢሮ

የማይበልጥ ከሆነ የክፍያው ልክ በቢሮ ኃላፊው ሊፀድቅ ይችላል።

## 22. ማሳወቅ

የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የፀደቁ አዳዲስ የዕቃና የአገልግሎት ዋጋዎች እንዲሁም በነባር ዋጋዎች ላይ የተደረጉና የፀደቁ ማሻሻያዎችን ዝርዝር የሚፀኑበት ቀን ጭምር ለህ/ሰቡ ማሳወቅ አለባቸው።

## 23. መመርመር

የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከቢሮው በሚወጣው መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ልዩነት የዕቃና የአገልግሎት ዋጋ መጠን ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ግምገማ ማካሔድ አለባቸው።

# ክፍል አምስት

## የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰብና ገቢ ማድረግ

## 24. የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰብ

የመንግሥት ገንዘብ ለመሰበሰብ በሕግ ግዴታ ያለው የእያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለመንግሥት ሥርዓት መኖሩን እና የመንግሥት ገንዘብ በሚገባ መሰብሰቡን ማረጋገጥ አለበት።

## 25. የመንግሥት ገንዘብ ስለመቀበል

1. በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ስም የሚሰበሰብ ማናቸውም ገንዘብ ተከታታይ ቁጥር ያለው በቢሮው

www.abyssinialaw.com



ሓላፊ ወይ ድማ ብቢሮ ሓላፊ ብዝተውሃቦ ውክልና መሰረት ዝተዳለወ ሕጋዊ ቅብሊት ክወሃብ አለዎ።

2. ዝኾነ ተመላሲ ገንዘብ ብጥረ ገንዘብ ፣ ብቼክ ወይ ድማ ብባንኪ ዝውውር ካብ'ቲ ቢሮ ወይ ድማ ካብ ካልእ መንግስታዊ ቤት ፅዮ ዝተዛወረ ገንዘብ ሓዊሱ ፣ ተቐባሊ ሕጋዊ ቅብሊት ክህብ አለዎ።

3. በዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1ን 2ን ዝተሓገገ እንተሃለወ'ውን ኣብ ባንኪ ሒሳብ መንግስቲ ኣታዊ ንዝተገበረ ገንዘብ ቅብሊት ባንኪ እኹል ይኸውን፡፡

## 26. ገንዘብ ሓደራ ወይ ትሕጃ

1. ካብ ቤት ፍርዲ ወይ ኣግባብ ካብ ዘለዎ ቤት ፅዮ ብዝወሃብ ትእዛዝ፣ምስ ትካላትን ውልቀ ሰባትን ብዝገብርዎ ስምምዕነት ወይ ንኣፈፃፅማ ዕድጊት ብዝሕተት ውሕስና መሰረት መንግስታዊ ኣብያተ ፅዮ ብሽም ትካላት ወይ ድማ ውልቀ ሰባት ገንዘብ ብሓደራ ወይ ብትሕጃ ብጊዚያዊነት ተቐቢሎም ንምዕናሕ ወይ ንምምሕዳር ይኽእሉ እዮም።

2. መንግስታዊ ኣብያተ ፅዮ ብሓደራ ወይ ድማ ብትሕጃ ዝተቐበልዎ ገንዘብ ሒሳብ ሃፍቲ ክልላዊ መንግስቲ ካብ ዝኾነ ገንዘብ ፈልዮም ብዝተፈለየ ሒሳብ መደብ ክምዝግብዎ አለዎም።



ኃላፊ ወይም በቢሮ ኃላፊው በተሰጠ ውክልና መሠረት የተዘጋጀ ሕጋዊ ደረሰኝ መሰጠት አለበት።

2. ማናቸውም ተመላሽ ገንዘብ ፣ በጥሬ ገንዘብ ፣ በቼክ ወይም በባንክ ዝውውር ከቢሮው ወይም ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተዘዋውረው ገንዘብ ጭምር፣ ተቀባዩ ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም በመንግስት የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገ ገንዘብ የባንክ ደረሰኝ በቂ ይሆናል፡፡

## 26. የአደራ ወይም የመያዣ ገንዘብ

1. ከፍርድ ቤት ወይም አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ፣ ከድርጅቶቹ ወይም ግለሰቦች ጋር በሚያደርጉት ስምምነት ወይም ለግዥ አፈፃፀም በሚጠየቅ ዋስትና መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በድርጅቶች ወይም በግለሰቦች ስም የአደራ ወይም የመያዣ ገንዘብ በጊዜያዊነት ተቀብለው ለማቆየት ወይም ለማስተዳደር ይችላሉ።

2. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በአደራ ወይም በመያዣ የተቀበሉትን ገንዘብ ሂሣብ የክልል መንግሥቱ ሃብት ከሆነው ገንዘብ ለይተው በተለየ የሂሳብ መደብ መመዝገብ አለባቸው።

www.abyssinialaw.com



## 27. ብቼክ ዝእከብ ገንዘብ

ኣብ ውሽጢ ትግራይ ዘሎ ባንኪ ዘውፅኦ ቼክ ንቐፃሊ ዝኽፈል ክሳብ ዘይኮነን ንተቐባሊ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ንክኽፈል ዝተአዘዘ ክሳብ ዝኾነ እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ንኽፍሊት ተቐባልነት ክህልዎ ይኽእል። ተቐባልነት ዝረኸበ ቼክ ሽም 'ቲ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ዝገልፅ "ኣብ ውሽጢ ዝተጠቓለለ ፈንድ ኣታዊ ንምግባር ጥራሕ" ብዝብል ሓረግ ኣጠቓቕምኡ ዝውስን ምልክት ክግበረሉ ይግባእ።

## 28. ካብ ንብረት መንግስቲ ዝርከብ ኣታዊ

1. ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ካብ ንብረት መንግስቲ ኣታዊ ዝእከብ እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ክኸውን አለዎ።

2. ኣታዊ ዝረኸበ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ብዝረኸቦ ኣታዊ ንኽጥቀም ክሳብ ዘይተፈቕደሉ ብንብረት መንግስቲ ብምግልጋል ወይ ድማ ንብረት መንግስቲ ብምውጋድ ዝተረኸበ ዝኾነ ኣታዊ ኣብ ውሽጢ ዝተጠቓለለ ፈንድ ኣታዊ ክኸውን አለዎ።

## 29. ኣታዊ ብዛዕባ ምግባር

1. ዝኾነ ካብ ኣካቢ ገንዘብ ወይ ድማ ካብ ዝኾነ ካልእ መንግስታዊ ገንዘብ ዝእከብ ወይ ድማ ዝቕበል ሰብ በብመዓልቱ ወይ በቲ ቢሮ ብዝወፅእ መምርሒ ብዝምልከቶ ፍሉይ አሰራርሓ መሰረት ዝኣከቦ ገንዘብ ኣታዊ ክገብር አለዎ።

## 27. በቼክ ሚሰበሰብ ገንዘብ

በትግራይ ውስጥ ያለ ባንክ የሚያወጣው ቼክ ለወደፊት የሚከፈል እስካልሆነ እና ለተቀባዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንዲከፈል የታዘዘ እስከሆነ ድረስ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለክፍያ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል። ተቀባይነትን ያገኘ ቼክ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ስም የሚገልፅ "በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ ለማድረግ ብቻ" በሚል ሀረግ አጠቃቀሙን የሚገድብ ምልክት ሊደረግበት ይገባል።

## 28. ከመንግሥት ንብረት የሚገኝ ገቢ

1. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከመንግሥት ንብረት ገቢ የሚሰበሰበው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መሆን አለበት።

2. ገቢ ያገኘ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በገቢው መጠቀም እስካልተፈቀደለ ት በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥትን ንብረት በማስወገድ የተገኘ ማናቸውም ገቢ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት።

## 29. ገቢ ስለማድረግ

1. ማናቸውም ከገንዘብ ሰብሳቢ ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው የመንግሥት ገንዘብ የሚሰበስብ ወይም የሚቀበል ሰው በየቀኑ ወይም በቢሮው በሚወጣው መመሪያ በሚመለከተው ልዩ አሠራር መሠረት የሰበሰበውን ገንዘብ ገቢ ማድረግ አለበት።

www.abyssinialaw.com



2. ኣታዊ ዝግበር ገንዘብ ኩሉ ኣታዊ በጀት እንትኸውን እቲ ገንዘብ ናብ ዝኣከቦ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ባንኪ ሒሳብ ወይ ድማ ብኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ወይ ድማ ብሄራዊ ባንኪ ብዝስይሞም ባንኪታት ኣብ ዝርከብ ናይ'ቲ ቢሮ ባንኪ ሒሳብ ውሽጢ ኣታዊ ክግበር ኣለዎ።

3. ንብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ወይ ድማ እቲ ገንዘብ ኣታዊ ዝግበረሉ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ዝተጠቓለለ ፈንድ ንክኽፈል ዘይተኣዘዘ ቼክ፣ ሓዋላን ተስፋ ሰነድን ኣታዊ ክግበር ኣይክእልን።

30. <u>ምዝገባ</u>

1. በዚ ደንቢ ዓንቀፅ 24 ን 25ን መሰረት ዝግበር ምዝገባ ቅብሊታት ዝፍፀም እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ይኸውን።

2. ብኣዋጅ ቁፅሪ 173/2002 ዓንቀፅ 39 ካብ ዝተመልከተ ተመላሲ ወፃኢ እንተዘይኮይኑ ተኣካቢ ገንዘብ መንግስቲ ብኣታዊነት ክምዝገብ ኣለዎ።

## <u>ክፍሊ ሽዱሽተ</u>
## <u>ቅድመ ክፍሊታት</u>

31. <u>ንዕደጋ ሰራሕተኛታት ዝወሃቡ ቅድመ ክፍሊታት</u>

1. ዕድጊት ንምፍፃም ኣድላይ ኾይኑ እንተ ርከብ ንሰራሕተኛ እቲ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ቅድመ ክፍሊት ጥረ ገንዘብ ክግበር ይኽእል።

2. ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ሁሉ የበጀት ገቢ ሲሆን ገንዘቡን በሰበሰበው የመንግሥት መሥሪያቤት የባንክ ሂሣብ ወይም ኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ወይም ብሄራዊ ባንክ በሚሰይማቸው ባንኮች በሚገኘው የቢሮው የባንክ ሂሣብ ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት።

3. ለትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ወይም ገንዘቡ ገቢ ለሚደረግለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተጠቃለለ ፈንድ እንዲከፈል ያልታዘዘ ቼክ፣ የሀዋላ ሰነድ እና የተስፋ ሰነድ ገቢ ሊደረግ አይችልም።

30. <u>ምዝገባ</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 24 እና 25 መሠረት የሚደረገው የደረሰኞች ምዝገባ የሚከናወነው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

2. በአዋጅ ቁጥር 173/2002 አንቀጽ 39 ከተመለከተው የተመላሽ ወጪ በስተቀር ማናቸውም ተሰብሳቢ የመንግሥት ገንዘብ በገቢነት መመዝገብ አለበት።

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የቅድሚያ ክፍያዎች</u>

31. <u>ለግዢ ሠራተኞች ስለሚሰጡ የቅድሚያ ክፍያዎች</u>

1. ግዢ ለመፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለምንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ የጥሬ ገንዘብ የቅድሚያ ክፍያ ሊደረግ ይችላል።

www.abyssinialaw.com



ከምዚ ዝበለ ቅድመ ክፍሊት ላዕለዋይ ሓላፊ እቲ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ክሳብ ዘይፈቐደ እቲ ሰራሕተኛ ካብ ዝተዋህቦ ዕለት ጀሚሩ ኣብ ውሽጢ ሽውዓተ ናይ ስራሕ መዓልቲ ክፍሊቱ ክወራርድ ኣለዎ።

2. ላዕለዋይ ሓላፊ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ወይ ድማ እቲ ሓላፊ ብፅሑፍ ዝወከሎ ሰራሕተኛ ዝለዓለ መጠን ቅድመ ክፍሊት ይውሰን። ንዝለዓለ መጠን ቅድመ ክፍሊት ንምውሳን ክማልኡ ዘለዎም ቅድመ ኩነታት ክማልኡ ክምዘለዎም እቲ ቢሮ ኣብ ዘውፅኦ መምርሒ ይውሰን።

## 32. ንመጓዓዓዝን ኣበልን ብዛዕባ ዝግበር ቅድመ ክፍሊት

1. ኣብ ውሽጢ ሓደ በጀት ዓመት ብተኸታታሊ ልዕሊ ሰለስተ ወርሒ ክፍሊት ውዕሎ ኣበል ምፍፃም ኣይከኣልን። ኮይኑ ግና ላዕለዋይ ሓላፊ ዘቕርቦ ሕቶ ብብቑዕ ምኽንያት ዝተደገፈ'ዩ ኢሉ እንተኣምን ናይ'ቲ ቢሮ ሓላፊ ውዕሎ ኣበል ልዕሊ ዝተጠቐሰ ግዜ ንክኽፈል ክፈቅድ ይኽእል።
2. ኣከፋፍላ ውዕሎ ኣበልን መጓዓዓዝን ቅድመ ክፍሊት ኣፈፃፅማ እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ይፍፀም።

## 33. ወሰን ቅድመ ክፍሊት

ቅድመ ክፍሊት ዝተውሃቦ ሰራሕተኛ መንግስቲ ካብኡ ዝድለ ሒሳብ ቅድመ ክፍሊት ክሳብ ዘየወራረደ ወይ ዘይተከአ ዋላ ሓንቲ ቅድመ ክፍሊት ኣይወሃቦን።



ሠራተኛው እንዲህ ያለውን የቅድሚያ ክፍያ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ካልፈቀደ በስተቀር ክፍያው ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ማወራረድ አለበት።

2. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ኃላፊው በጽሑፍ የወከለው ሠራተኛ የቅድሚያ ክፍያውን ከፍተኛ መጠን ይወስናል። የቅድሚያ ክፍያን ከፍተኛ መጠን ለመወሰን ምን ምን ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## 32. ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ ስለሚደረግ የቅድሚያ ክፍያ

1. በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በተከታታይ ከሦስት ወር በላይ የውሎ አበል ክፍያ መፈፀም አይቻልም። ሆኖም ከመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የቀረበው ጥያቄ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ነው ብሎ ሲያምን የቢሮ ኃላፊው የውሎ አበል ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ እንዲከፈል ሊፈቅድ ይችላል።
2. የውሎ አበልና የመጓጓዣ አበል የቅድሚያ ክፍያ አፈፃፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል።

## 33. የቅድሚያ ክፍያ ገደብ

የቅድሚያ ክፍያ የተሰጠው የመንግስት ሠራተኛ የሚፈለግበትን የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ እስካላወራረደ ወይም እስካልተካ ድረስ ምንም ዓይነት የቅድሚያ ክፍያ አይሰጠውም።

www.abyssinialaw.com





34. **ቅድመ ክፍሊታት ክምለሱ ምግባር**

1. ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ሰራሕተኛ ብመሰረት 'ዚ ደንቢ ዝተዋህቦ ቅድመ ክፍሊት ብሙሉእ ወይ ብኽፋል ኸይከፈለ ወይ ከየወራረደ እንተደአ ተሪፉ እቲ ዘይተኸፈለ ሒሳብ ቅድመ ክፍሊት ብዘይካ ካብ ጡረታ ኣበል ክልል መንግስቲ ነቲ ሰራሕተኛ ካብ ዝኸፍሎ ዝኾነ ገንዘብ ክቕንስ ወይ ክትካእ ይካኣል።

2. ዝኾነ ሰራሕተኛ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ብመሰረት'ዚ ደንቢ ዝተዋህቦ ቅድመ ክፍሊት ብምልኡ ወይ ብኽፋል ከየወራረደ ወይ ከይመለሰ እንተሞይቱ እቲ ዘይተመለሰ ሒሳብ ቅድመ ክፍሊት ብዘይካ ካብ ጥሮታ ኣበልን ኣብ ኣዋጅ ሰራሕተኛታት መንግስቲ ብዝተሓገገ መሰረት እቲ ሰራሕተኛ መንግስቲ ኣብ ዝሞተሉ ግዜ ንቤተሰቡ ዝኽፈል ገንዘብን ክልል መንግስቲ ንወረስቲ እቲ ሰራሕተኛ ካብ ዝኸፍሎ ዝኾነ ገንዘብ ክቕነስ ወይ ክትካእ ይካኣል።

3. ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ዘይተኸፈሉ ቅድመ ክፍሊታት ኣድላዪ ስጉምቲ ምውሳድ ንኽከኣል ኣብ መወዳእታ ሕድሕድ ወርሒ ዘይተኸፈሉ ቅድመ ክፍሊታት ኩሎም ከፃሪ ኣለዎ።

4. ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ብፍቓዶም ስርሖም ዝለቁ ወይ ጥሮታ ዝወፁ ሰራሕተኛታት ናይ መወዳእታ ግዜ ክፍሊት

34. **የቅድሚያ ክፍያዎችን ስለማስመለስ**

1. ማናቸውም መንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን የቅድሚያ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይከፍል ወይም ሳይወራረድ ቢቀር ያልተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ ከጡረታ አበል በስተቀር የክልሉ መንግሥት ለሠራተኛው ከሚከፍለው ማናቸውም ገንዘብ ላይ ሊቀነስ ወይም ሊተካ ይችላል።

2. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን የቅድሚያ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ሳያወራርድ ወይም ሳይመልስ ቢሞት፣ ያልተመለሰው የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብ ከጡረታ አበል እና በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ በተደነገገው መሰረት የመንግሥት ሠራተኛ በሚሞትበት ጊዜ ለቤተሰቡ ከሚከፈል ገንዘብ በስተቀር የክልሉ መንግስት ለሰራተኛው ወራሾች ከሚከፈለው ማናቸውም ገንዘብ ላይ ሊቀንስ ወይም ሊተካ ይችላል።

3. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ባልተከፈሉ የቅድሚያ ክፍያዎች ላይ አስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ያልተከፈሉ የቅድሚያ ክፍያዎችን ሁሉ ማጣራት አለበት።

4. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የሚለቁ ወይም ጡረታ የሚወጡ ሠራተኞች የመጨረሻውን

www.abyssinialaw.com



መሃያ ቅድሚ ምርካቦም ዝወሰድዎ ቅድመ ክፍሊት ዝመለሱ ምዃኖም ክረጋግፅ አለዎ።

5. ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ፅዮ በጀት ዓመት ምስተወደአ ቀፂሉ ኣብ ዘሎ ወርሒ ዝተማልአ ዘይተኸፈለ ዝርዝር ቅድመ ክፍሊት መግለፂ የዳሉ። እዚ ዝርዝር መግለፂ ክምለሱ ዘይክእሉ ዘይተኸፈሉ ቅድመ ክፍሊታት ብምፍላይ ክምለሱ ዘይካኣልሉ ምኽንያት ምስ ዘርኢ ሓፂር መግለፂ ክቐርብ ዘለዎ ኾይኑ፣ ቅዳሑ እቲ በጀት ዓመት ካብ ዝተወደአሉ ኣብ ውሽጢ ክልተ ወርሒ ናብቲ ቢሮ ክለኣኽ አለዎ ።

35. <u>መዛግብቲ፡</u>

ሕድሕድ መንግስታዊ ቤት ፅዮ ቅድመ ክፍሊት ሒሳብ ብዝምልከት ግቡእን ዝተማልአን ሒሳብ መዝገብ ክሕዝ አለዎ።

36. <u>ፀብፃብ ምቕራብ</u>

ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ፅዮ እቲ ቢሮ ብዘውፅኦ መምርሒ መሰረት ኣብ መወዳእታ ሕድሕድ በጀት ዓመት ዘይተኸፈሉ ናይ ዝኾኑ ቅድመ ክፍሊት ፀብፃብ ምስ ዝተወደአ ናይቲ በጀት ዓመት ሒሳብ ፀብፃብ ክቐርብ አለዎ።

ጊዜ ደመወዝ ክፍያ ከማግኘታቸው በፊት የወሰዱት የቅድሚያ ክፍያ መመለሱን ማረጋገጥ አለበት።

5. ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበጀት ዓመቱ ካለቀ ቀጥሎ ባለው ወር የተሟላ ያልተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ዝርዝር መግለጫ ያዘጋጃል። ይህ ዝርዝር መግለጫ ሊመለሱ የማይችሉ ያልተከፈሉ የቅድሚያ ክፍያዎችን በመለየት ሊመለሱ ያልቻሉበትን ምክንያት ከሚያሣይ አጭር መግለጫ ጋር መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ግልባጭ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሁለት ወራት ውስጥ ለቢሮው መላክ አለበት።

35. <u>መዛግብት</u>

እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የቅድሚያ ክፍያ ሂሣብን የሚመለከት ተገቢና የተሟላ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት።

36. <u>ሪፖርት ማቅረብ</u>

ማናቸውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በእያንዳንዱ በጀት ዓመት መጨረሻ ያልተከፈሉ ማናቸውንም የቅድሚያ ክፍያዎች ሪፖርት ከተጠናቀቀው በጀት ዓመት ሂሣብ ሪፖረት ጋር ማቅረብ አለበት።

www.abyssinialaw.com



## ክፍሊ ሸውዓተ

## ተአከብቲ ሒሳባት፣ ግቡኣትን ሕቶታት ይግበኣንን ካብ መዝገብ ብዛዕባ ምስራዝ

37. ስልጣን ካብ መዝገብ ምስራዝ

1. ላዕለዋይ ሓላፊ ወይ ሓላፊ ወኪሉ እቲ ምክትል ሓላፊ መንግስታዊ ቤት ዕዮ ነቲ ዋኒን ኣግባብ ካብ ዘለዎ ክፍሊ ስራሕ ብዝቐርበሉ ሪኢቶ መሰረት ካብ ብር ዓሰርተ ሽሕ ዘይበልፅ ገንዘብ ዝሓዞ ሕድሕድ ሰነድ ካብ መዝገብ ናይ ምስራዝ ስልጣን ዝተዋህቦ ኾይኑ በዚ ዓይነት ካብ መዝገብ ዝስረዝ ሒሳብ ኣብ ውሽጢ ሓደ በጀት ዓመት ካብ ብር ሓምሳ ሽሕ ክበልፅ ኣይኽእልን።

2. ናይቲ ቢሮ ሓላፊ ካብ ላዕለዋይ ሓላፊ መንግስታዊ ቤት ዕዮን ኣግባብ ካብ ዘለዎ ናይ'ቲ ቢሮ ክፍሊ ስራሕን ብዝቐርበሉ ሪኢቶ መሰረት ካብ ብር ዓሰርተ ሽሕ ክሳብ ብር ሚኢቲ ሽሕ ገንዘብ ዝሓዘ ንሕድ ሕድ ሰነድ ካብ መዝገብ ምስራዝ ስልጣን ዝተዋህቦ ኾይኑ በዚ ዓይነት ካብ መዝገብ ዝስረዝ ሒሳብ ኣብ ውሽጢ ሓደ በጀት ዓመት ካብ ብር ሓደ ሚልዮን ክበልፅ ኣይኽእልን።

3. ንኽስረዝ ሪኢቶ ዝቐረበሉ ሕድሕድ ሒሳብ ዝሓዞ ገንዘብ ካብ ብር ሚኢቲ ሽሕ ዝበልፅ እንትኾውን ብስራሕ ፈፃሚ እቲ ክልል ውሳነ ንኽወሃበሉ ካብ ዝምልከቶ ላዕለዋይ ሓላፊ መንግስታዊ ቤት ዕዮን ካብ እቲ ቢሮ ሓላፊ ዝተዋሃበ ሪኢቶ ከምኡ'ውን ንውሳኔ ኣወሃህባ ኣድለይቲ ምስ ዝኾኑ መረዳእታታት ይመሓላለፍ



## ክፍል ሰባት

## ተሰብሳቢ ሂሣቦች፣ ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን ከመዝገብ ስለመሠረዝ

37. ከመዝገብ የመሠረዝ ሥልጣን

1. የመንግስት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ኃላፊውን በመወከል ምክትል ኃላፊው በጉዳዩ ኣግባብ ካለው የስራ ክፍል በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከብር አሥር ሺህ የማይበልጥ ገንዘብ የያዘውን እያንዳንዱን ሰነድ ከመዝገብ የመሠረዝ ስልጣን የተሰጠው ሲሆን በዚህ ዓይነት ከመዝገብ የሚሠረዘው ሂሣብ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር ሃምሣ ሺህ ሊበልጥ አይችልም።

2. የቢሮ ኃላፊው ከመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ኣግባብ ካለው የቢሮው የስራ ክፍል በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ከብር አሥር ሺህ እስከ ብር መቶ ሺህ የያዘውን እያንዳንዱን ሰነድ ከመዝገብ የመሰረዝ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን፣ በዚህ ዓይነት ከመዝገብ የሚሰረዘው ሂሣብ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር አንድ ሚልዮን ሊበልጥ አይችልም ፡፡

3. እያንዳንዱ እንዲሰረዝ አስተያየት የቀረበበት ሂሣብ የያዘው ገንዘብ ከመቶ ሺ ብር የሚበልጥ ከሆነ፣ በክልሉ ካቢኔ ውሳኔ እንዲሰጥበት ከሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ እና ከቢሮ ኃላፊው አስተያየት እንዲሁም ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች ጋር ይተላለፋል።

## 38. ስረዛ ዕዳ ሰራሕተኛታት

1. ብክልል መንግስቲ ንሰራሕተኛታት ልዕሊ ግቡእ ዝተኸፈለ መሃያ ወይ ምስ ቁፃር ብዝተተሓሓዘ አበል ምኽንያት ዝድለ ዝኾነ ተኣካቢ ሒሳብ ግቡእ ወይ ድማ ሕቶ ይግበኣኒ በቲ ቢሮ ሓላፊ እንተዘይፀዲቑ ካብ መዝገብ ክስረዝ ኣይክእልን።
2. ኣብ'ዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተመልከተ እንተሃለወ'ውን ካብ ስራሕ እንተተሰናቢቶምን ክኽፈሎም ዝግባእ ዝኾነ ክፍሊት ድሕሪ ምፍፃም ካብ ሰራሕተኛታት ብናይቲ ክልል መንግስቲ ዝድለ ዝኾነ ተኣካቢ ሒሳብ ግቡእ ወይ ሕቶ ይግበኣኒ ብዝምልከት ካብ መዝገብ ምስራዝ መትከል ተፈፃሚ ይኸውን።

## 39. ፀብፃብ ናይ ምቕራብ ግቡእ

1. ሕድሕድ መንግስታዊ ቤት ዕዮ በብወርሑ መወዳእታ ተኣካቢ ሒሳባት፣ ግቡኣትን ሕቶታት ይግበአንን ብዝምልከት ዝተማልአ መግለፂ ክዳሉን ናይ'ዚ ቅዳሕ ነቲ ቢሮ ክልእኽን አለዎ። እዚ መግለፂ'ውን ኣታዊ ክኾኑ ዘይኽእሉ ተኣከብቲ ሒሳባት ግቡኣትን ሕቶታት ይግበአንን ፈልዩ ዘርእን ኣብዚ ውሳኔ'ዚ ንምብፃሕ ዝተኻእለሉ ምኽንያት ዘርዚሩ ብዘርኢ ሓፂር መግለፂ ዝተደገፈ ክኸውን አለዎ።
2. ብአዋጅ ቁፅሪ 173/2002 ዓንቀፅ 5 ንቢሮ ትልምን ፋይናንስን ብዝተዋሀበ ስልጣን መሰረት ዝወፅእ መምርሒ ብምኽታል መንግስታዊ ኣብያተ ዕዮ በብወርሑ መወዳእታ ኣብ መዝገቦም ዝረአ ተኣካቢ ሒሳብ፣ ግቡእን ሕቶ

## 38. የሠራተኞች የዕዳ ስረዛ

1. በክልሉ መንግሥት ለሠራተኞች ከተገቢው በላይ ከተከፈለ ደመወዝ ወይም ከቅጥር ጋር በተያያዘ አበል ምክንያት የሚፈለግ ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሣብ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ በቢሮ ኋላፊው ካልፀደቀ በስተቀር ከመዝገብ ሊሰረዝ አይችልም።
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተመለከተው ቢኖርም ከሥራ ከተሰናበቱ እና ሊከፈላቸው የሚገባ ማናቸውም ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ከሠራተኞች በክልሉ መንግሥት የሚፈለግን ማናቸውንም ተሰብሳቢ ሂሳብ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ በሚመለከት ከመዝገብ የመሰረዝ መርህ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 39. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

1. እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየወሩ መጨረሻ ተሰብሳቢ ሂሣቦች፣ ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን በሚመለከት የተሟላ መግለጫ ማዘጋጀት እና የዚህኑ ግልባጭ ለቢሮው መላክ አለበት።ይህም መግለጫ ገቢ ሊሆኑ የማይችሉትን ተሰብሳቢ ሂሳቦች ግዴታዎች እና የይገባኛል ጥያቄዎች ለይቶ የሚያሳይና ከዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የተቻለበትን ምክንያት በሚዘረዝር አጭር መግለጫ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 173/2002 አንቀጽ 5 ለፕላንና ፋይ/ቢሮ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚወጣውን መመሪያ በመከተል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በየወሩ መጨረሻ በመዝገባቸው የሚታየውን ተሰብሳቢ ሂሣብ፣ ግዴታ እና

www.abyssinialaw.com



ይግበኣኒን ነዚ ቢሮ ፀብፃብ ናይ ምቕራብ ክምኡ'ውን በብዓመቱ መወዳእታ ኣብ መዝገቦም ዝረአ ተኣካቢ ሒሳብ ግቡእን ሕቶ ይግበኣንን ናይ ሕሉፍ በጀት ዓመት ናይ መንግስቲ ሒሳብ ናይ ምፅብፃብ ግቡእ ኣለዎም።

3. ልዕል ኢሉ ካብ ዝተገለፀ ብተወሳኺ ዝኾነ መንግስታዊ ቤት ፅዮ ካብ መዝገብ ዝተሰረዘ ተኣካቢ ሒሳብ ግቡእን ሕቶ ይግበኣንን በብወርሑ ነቲ ቢሮ ብምፅብፃብ ክምኡ'ውን ኣብ ሕሉፍ በጀት ዓመት ካብ መዝገብ ዝተሰረዘ ተኣካቢ ሒሳብ ግቡእ ወይ ድማ ሕቶ ይግበኣኒ በቲ ዓመት ንሱ ወይ ድማ ኣብ ዝሓለፈ ዓመታት ዝተፈፀመ ምዃኑን ብምፍላይ ክፅብፅብ ኣለዎ።

## ክፍሊ ሸሞንተ
## ልቓሕ መንግስቲን ገንዘብ መንግስቲ ኢንቨስት ምግባርን

### 40. ስትራተጂ ምምሕዳር ልቓሕ

1. እቲ ሓላፊ ቢሮ ተደላይ መጠን ገንዘብ ኣብ ግቡእ እዋን ምልቃሕ ሓፈሻዊ ፅላማ መሰረት ብምግባር ወፃኢ ብዝቕንስ መንገዲ ንምምራሕ ክምኡ'ውን ኩነታት ልቓሕ ፅዕንቶ ዕዳ ናይ ምኽፋል ዓቕሚን መሰረት ብዝገብር መንገዲ ምውሳድ ዘኽእል ስትራተጂ ምምሕዳር ልቓሕ ክዳሉ ኣለዎ፡፡

2. ልቓሕ ኣብ ዝውሰደሉ ግዜ ካብ ወለድ ወፃኢ ዝኾኑ ዝተፈላለዩ ምስ ልቓሕ ዝተተሓሓዙ ወፃኢታት ኣብ ግምት ውሽጢ ክኣትው ኣለዎም። ክምዚኦም ዝበሉ ወፃኢታት

የይገባኛል ጥያቄ ለቢሮው ሪፖርት የማድረግ እንዲሁም በየዓመቱ መጨረሻ በመዝገባቸው የሚታየውን ተሰብሳቢ ሂሣብ ግዴታ እና የይገባኛል ጥያቄ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ውስጥ የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

3. ከዚህ በላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከመዝገብ የተሰረዘውን ተሰብሳቢ ሂሣብ ግዴታ እና የይገባኛል ጥያቄ በየወሩ ለቢሮው ሪፖርት በማድረግ እንዲሁም በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ከመዝገብ የተሰረዘውን ተሰብሳቢ ሂሣብ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ በዚያው ዓመት ወይም ባለፉት ዓመታት የተፈፀመ መሆኑን በመለየት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

## ክፍል ስምንት
## በመንግሥት ብድር እና የመንግሥትን ገንዘብ ኢንቨስት ስለማድረግ

### 40. የብድር ኣስተዳደር ስትራተጂ

1. የቢሮ ሐላፊው ተፈላጊውን የገንዘብ መጠን በተገቢው ጊዜ የመበደርን አጠቃላይ አላማ መሠረት ያደረገ እና ወጪን በሚቀንስ መንገድ ለመምራት እንዲሁም ብድር የዕዳ ጫና እና የመክፈል አቅምን መሠረት ባደረገ ኣኳሃን መውሰድ የሚያስችል የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ማዘጋጀት አለበት።

2. ብድር በሚወስድበት ግዜ ከወለድ ውጪ የሆኑ የተለያዩ ከብድሩ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። የዚህ ዓይነቶቹ ወጪዎች የተለያዩ

www.abyssinialaw.com



ዝተፈላለዩ ኮምሽናት፣ ክፍሊታት ናይ ሬጂስትራራትን ወኪላት ፋይናንስን ወፃኢታት ምምሕዳር ይውስኹ።

3. ልቓሕ ኣብ ልዕሊ ናይቲ ክልል ኢኮኖሚ ኣሉታዊ ዝኾነ ውፅኢት ዘስዕቡን ዘይምርግጋእ ዝፈጥሩ ኹነታትን ምክልኻል ብዝኽእል መንገዲ ክመሓደር ይግበኦ።

4. ልቓሕ ሓፂር እዋን እቲ ክልል ብባንኪታትን ብውሽጢ ምንቅስቓስ ልውውጥ ዕዳጋ ዘሎ ሚዛን ሒሳብ ከምኡ'ውን ናይ እቶትን ግምት ወፃኢ በጀትን ብዝምልከት ዘተኣማምን እዋናዊ መረዳእታ መሰረት ብምግባር ክፍፀም ኣለዎ።

41. <u>መንግስቲ ዝወስዶ ልቃሕ፣</u>

ናይቲ ቢሮ ሓላፊ እቲ ዝፀደቐ ዓመታዊ ትልሚ ፋይናስ መሰረት ብምግባር ናይ'ቲ ክልል ድልየት ፋይናንስ ዘማልእ ናይ ውሳኔ ሓሳብ በብ ሽዱሽተ ወርሒ ንቤት ምኽሪ ስራሕ ፈፃሚ እቲ ክልል ኣቕሪቡ ክፀድቕ ይገብር። ብኸምዚ ዓይነት ዝቐርብ ናይ ውሳኔ ሓሳብ በቐጥታ ብምልቃሕ ወይ ድማ ናይ ውሕስና ሰነዳት ምውፃእን ምሻጥን ብዝኣመሰሉ ሜላታት ዝእከብ ምዃኑ ዝገልፁ መረዳእታታት ክሕዝ ኣለዎ።

42. <u>ስልጣን ምቁፅፃር ቢሮ ሓላፊ፡-</u>

ሓላፊ እቲ ቢሮ ትካላት ልምዓትን ትካላት ፋይናንስን እቲ ክልልን ካብ ውሽጢ ሃገር ልቓሕ ዝወስድሉ ኩነታትን ኣፈፃፅማ እቲ ልቓሕን ይቆፃፀር፡፡



ኮሚሽኖችን፣ ክፍሎች፣ ሬጂስትራሮች እና የፋይናንስ ወኪሎችን የአስተዳደር ወጪዎች ይጨምራሉ።

3. ብድር በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ የሆነ ውጤት የሚያስከትሉና አለመረጋጋትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል በሚያስችል መንገድ መተዳደር ይኖርበታል።

4. የአጭር ጊዜ ብድር ክልሉ በባንኮች እና በገበያ ልውውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን የሂሣብ ሚዛን እንዲሁም የገቢ እና የወጪ በጀትን ግምት በሚመለከት ኣስተማማኝ የሆነ ወቅታዊ መረጃን መሠረት በማድረግ መፈፀም አለበት።

41. <u>መንግሥት የሚወስደው ብድር፣</u>

የቢሮ ኃላፊው ያፀደቀውን ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የክልሉን የፋይናንስ ፍላጎት የሚያሟላ የውሳኔ ሃሣብ በየስድስት ወሩ ለክልሉ ካስራ አስፈፃሚ አቅርቦ ያስፀድቃል። በዚህ ዓይነት የሚቀርበው የውሳኔ ሃሣብ በቀጥታ በመበደር እና/ ወይም የዋስትና ሰነዶችን ማውጣትና መሸጥን በመሳሰሉ ዘዴዎች የሚሰበሰብ መሆኑን የሚገልፁ መረጃዎችን መያዝ አለበት።

42. <u>የቢሮ ኋላፊው የመቆጣጠር ስልጣን፡-</u>

የቢሮ ኃላፊው የክልሉ የልማት ድርጅቶች እና የፋይናንስ ተቋማት ከአገር ውስጥ ብድር የሚወስዱበትን ሁኔታ እና የብድሩን አፈፃፀም ይቆጣጠራል፡፡

www.abyssinialaw.com



## 43. ኢንቨስትመንት

ኣብ ውሽጢ ዝተጠቓለለ ፈንድ ዝርከብን ኣብ ውሽጢ ሓጺር እዋን ንኽፍሊት ዘይድለ ገንዘብ ኣብ ልዕሊ ሰነዳት ውሕስና ኢንቨስት ክግበር ዝኽእል ሓላፊ እቲ ቢሮ እዚ ገንዘብ ብርግፅ ንኽፍሊት ዘይድለ ትርፊ ገንዘብ ምዃኑን ዝሓሸ ጥቕሚ ስለ ዝርከቦ ንኻልእ ዕዳ መንግስቲ ናይ ምምሕዳር ተግባር ንኽውዕል ምግባር ዘይከኣል ምዃኑ እንተረጋገፅ ይኸውን።

## 43. ኢንቨስትመንት

በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የሚገኝ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለክፍያ የማይፈለግ ገንዘብ በዋስትና ሰነዶች ላይ ኢንቨስት ሊደረግ የሚችለው የቢሮ ኃላፊው ይህ ገንዘብ በእርግጥ ለክፍያ የማይፈለግ ትርፍ ገንዘብ መሆኑን እና የተሻለ ጥቅም ለሚያስገኝ ለሌላ የመንግሥት ዕዳን የማስተዳደር ተግባር እንዲውል ማድረግ የማይቻል መሆኑን ሲያረጋግጥ ይሆናል።

## 44. ፈንድ ጥሪት

1. ኣብ ነዊሕ እዋን ንክኽፈል ዝተወሰደ ልቓሕ ብመሰረት ፋይናንስ ኣዋጅ ቁፅሪ 173/2002 ዓንቀፅ 49 ምጥያሽን ምምሕዳርን ጥሪት ፈንድ መተካእታ ንብረታት መሰረት ስራሕ ፈፃሚ እቲ ክልል ንዝወሰኖም ካልኦት ዋኒናት ዝውዕል ናይ ጥሪት ፈንድ ክምስረት ይኽእል።
2. ፈንድ ጥሪት ክምስረት ዝኽእል ፈፃሚ ስራሕ እቲ ክልል ኢኮኖምያዊ ረብሓ ዘለዎ ምዃኑ ምስ ዝአምነሉ ጥራሕ ይኸውን፡፡ ንካፒታል ንብረታት መተካእታ ዝውዕል ፈንድ ጥሪት ክተሓዝ ዝኽእል ንዝተተለመሉ ተግባር ንኽውዕል ጥራሕ'ዩ።
3. ፈንድ ጥሪት ናይ ምጥያሽ ተግባር ከም ሓደ ምንቅስቓስ ከዋፅእ ምኽኣሉ ምስ ትልሚ ፋይናንስን ትልሚ ልምዓት መንግስትን ብምትሕሓዝ ናይ'ቲ ፈንድ ምጥያሽ ዝህልዎ ጥቕሚ ብዘርኢ ዝርዝር ኩነታት ክድገፍ አለዎ።

## 44. ጥሪት ፈንድ

1. በረጅም ጊዜ እንዲከፈል የተወሰደ ብድር ለመክፈል፣ ለቋሚ ንብረቶች መተኪያ ወይም በፋይናንስ ኣዋጁ ቁጥር 173/2002 ኣንቀፅ 49 የንብረት ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር መሠረት የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ለሚወስንባቸው ሌሎች ጉዳዮች የሚውል የንብረት ፈንድ ሊቋቋም ይችላል።
2. ንብረት ፈንድ ሊቋቋም የሚችለው የክልሉ ስራ ኣፈፃሚ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲያምንበት ብቻ ይሆናል።ለካፒታል ንብረቶች መታከያ የሚውለው ንብረት ፈንድ ሊያዝ የሚችለው ለታቀደለት ተግባር እንዲውል ብቻ ነው።
3. ንብረት ፈንድ የማቋቋም ተግባር ቢያንስ እንደ ንግድ እንቅስቀሴ የሚያዋጣ መሆን ከፋይናንስ ዕቅዱና ከመንግሥት የልማት ዕቅድ ጋር በማያያዝ የፈንዱ መቋቋም የሚያስገኘውን ጥቅም በሚያሳይ ትንታኔ መደገፍ ኣለበት፡፡

www.abyssinialaw.com





እዚ ትንታነ ንግዲ ዝህልው መማረፂታት ኢንቨስትመንትን ዝተወሰደ መማረፂ ካብ ኩሉ ዝሓሸ ክኸውን ዝኽእለሉ ምኽንያትን ዘርኢ ክኸውን አለዎ።

4. ምምሕዳር ጥሪት ፈንድ ባዕሉ ዝኽአለ ስርዓት አመዘጋግባ ሒሳብን ምንቅስቓስ ጥሪት ፈንድን ቅድም ክብል ካብ ዝቐረበ ፀብፃብ ንዳሓር ዝተገበረ ለውጥን ኣብ ውሽጢ ዝተተለመሉ እዋን ከህልዎ'ዩ ተባሂሉ ዝግመት ዋጋ ብዘርኢ ኣብ ውሽጢ ዝተወሰነ እዋን ፈፃሚ ስራሕ እቲ ክልል ብዝቐርብ ፀብፃብ ክድገፍ አለዎ።

## 45. ምትሕልላፍ ዕዳ

ሓላፊ እቲ ቢሮ ክሳብ ዘየዕደቖ ዕዳ ሳልሳይ ወገን ውሽጢ ሃገር ወይ ድማ ካብ ሳልሳይ ወገን ዕዳ ውሽጢ ሃገር ናይ ምእካብ መሰል ንመንግስቲ እቲ ክልል ምትሕልላፍ ኣይከኣልን። ብኸምዚ ዓይነት ዝመሓላለፍ ዕዳ ተቐባልነት ዝረኸበ ምዃኑ ብፊርማ እቲ ሓላፊ ቢሮ ክረጋገፅ አለዎ። ናይ'ቲ ቢሮ ሓላፊ ምትሕልላፍ ተግባር ቅድሚ ምቕባሉ ብግቡእ መንገዲ ዝተረጋገፀ ሕጋዊ ሰነድ ክበፅሖ ይግባእ።

## 46. መዛግብትን ሒሳባትን

ሓላፊ ቢሮ ብመሰረት ኣዋጅ ቁፅሪ 173/2002 ዓንቀፅ 47 ምምሕዳር ዕዳ መንግስቲ ዝምልከት መዝገብን ስርዓት ኣተሓሕዛ ሒሳብን ንኽምስረት ይገብር።

እዚ ስርዓት'ውን እዞም ዝስዕቡ ዝሕዝ ወይ ዘርኢ ይኸውን።

ይህ የንግድ ትንታኔ የነበሩትን የኢንቨስትመንት ኣማራጮች እና የተወሰደው ኣማራጭ ከሁሉም የተሻለ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት የሚያሳይ መሆን ኣለበት፡፡

4. ንብረት ፈንድ ኣስተዳደር ራሱን የቻለ የሂሳብ አመዘጋገብ ሥርዓት እና የንብረት ፈንዱን እንቅስቃሴ ቀደም ሲል ከቀረበው ሪፖርት በኃላ የተደረገውን ለውጥ እና በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ይኖረዋል ተብሎ የሚገመተውን ዋጋ በሚያሳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ስራ ኣፈፃሚ በሚቀርብ ሪፖርት መደገፍ አለበት።

## 45. ዕዳን ስለማስተላለፍ

የቢሮ ሐላፊው ካላፀደቀው በስተቀር የሦስተኛ ወገን የአገር ውስጥ ዕዳን ወይም ከሦስተኛ ወገን የአገር ውስጥ ዕዳን የመሰብሰብ መብት ለክልሉ መንግስት ማስተላለፍ ኣይቻልም። በዚህ ዓይነት የሚተላለፍ ዕዳ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑ በቢሮ ሐላፊው ፊርማ መረጋገጥ አለበት። የቢሮ ሐላፊው የማስተላለፉን ተግባር ከመቀበሉ በፊት በተገቢው መንገድ የተረጋገጠ ሕጋዊ ሰነድ ሊደርሰው ይገባል።

## 46. መዝገቦች እና ሂሣቦች

የቢሮ ሐላፊው በአዋጅ ቁጥር 173/2002 ኣንቀጽ 47 መሠረት የመንግሥት ዕዳ ኣስተዳደርን የሚመለከት የመዝገብ እና የሂሣብ ኣያያዝ ሥርዓት እንዲመሰረት ያደርጋል።

ይህም ሥርዓት የሚከተሉትን የሚይዝ ወይም የሚያሳይ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com



1. ስራሕ ፈፃሚ እቲ ክልል ብልቓሕ ንኽውሰድ ዝተፈቐደ ዝኾነ ገንዘብ።
2. ብልቓሕ ዝተወስደ ዝኾነ ገንዘብ ዘርኢ መግለፂ።
3. ብልቓሕ ካብ ዝተወሰደ ገንዘብ ውሽጢ ዝተኸፈለ ቀንዲ ዕዳ ወለድ ወይከአ ካልኦት ክፍሊታት
4. ንኢንቨስትመንት ዝወዓለ ዝኾነ ገንዘብ መግለፂን
5. ካብ ኢንቨስትመንት ዝተረኸበ ኣታዊ ከምኡ'ውን እዞም ኢንቨስትመንታት ንምሓዝ፣ ምምሕዳርን ንምልቃቕን ዝተኸፈለ ገንዘብ።

## ክፍሊ ትሸዓተ
## ርክባት ፋይናንስ ክልልን ፌደራል መንግስትን

47. **ስርዓት ኣቀራርባ ፀብፃብ ፋይናንስ**

1. ስርዓት ኣቀራርባ ፀብፃብ ፋይናንስ ክልላዊ መንግስቲ ቤት ምኽሪ ሚኒስትራት ንኽማላእ ምስ ዝሓቶ ስርዓት ኣቀራርባ ፀብፃብ ፋይናንስ ዝተጠዓዓመ ክኸውን ኣለዎ።
2. መንግስቲ እዚ ክልል ብመሰረት ካብ ሚኒስተር ገንዘብን ኢኮኖሚያዊ ልምዓትን ዝረኸቦ ድጋፍ ምስ ፌደራል መንግስቲ ዘለዎ ርክብ ፋይናንስ ንምቅልጣፍ ዘኽእል ስርዓት ኣቀራርባ ፀብፃብ ፋይናንስ የጣይሽ፡፡



1. በክልሉ ስራ አስፈፃሚ በብድር እንዲወሰድ የተፈቀደውን ማናቸውንም ገንዘብ
2. በብድር የተወሰደውን ማናቸውንም ገንዘብ የሚያሳይ መግለጫ
3. በብድር ከተወሰደው ገንዘብ ውስጥ የተከፈለውን ዋና ዕዳ፣ ወለድ ወይም ሌሎች ክፍያዎች
4. ለኢንቨስትመንት የዋለውን ማናቸውንም ገንዘብ መግለጫ እና
5. ከእንቨስትመንት የተገኘውን ገቢ እንዲሁም እነዚህን ለኢንቨስትመንቶች ለመያዝ ለማስተዳደር እና ለማስለቀቅ የተከፈለውን ገንዘብ

## ክፍል ዘጠኝ
## የክልሉና የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ግንኙነቶች

47. **የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት**

1. የክልሉ መንግሥት የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲሟላ ከሚጠይቀው የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።
2. የክልሉ መንግስት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከሚያገኘው ድጋፍ መሠረት ከፌደራል መንግስት ጋር ያለውን የፋይናንስ ግንኙነት ለማቀላጠፍ የሚያስችል የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ያቋቁማል፡፡

www.abyssinialaw.com



3. መንግስቲ እዚ ክልል ቤት ምኽሪ ሚኒስትራት ዝሓቶ ብምምላእን ሚኒስትር ገንዘብን ኢኮኖሚ ልምዓትን ዘውፅኦ ቅጥዒ መሰረት በብወርሑ፣ ብርብዒ፣ ብመንፈቕን በብዓመቱን ፀብፃብ ፋይናንስ ንሚኒስቴር ገንዘብን ኢኮኖሚ ልምዓትን የቕርብ። እዚ ፀብፃብ እዚ'ውን ናይ'ዚ ክልል ኣታዊታትን ወፃኢታትን ብፍልፍሎምን ብሒሳብ መፍለይ ቁፅሪታቶምን ብምፍላይ ዘሎ ጥረ ገንዝብ መጠን ዘይተኸፈለ ዕዳን ኣፈፃፅማ ስርሖምን ዘርኢ ክኸውን ኣለዎ።

## 48. ውህደት ታክስ

ኣብ ናይ'ቲ ክልል መንግስቲ ሓደሽቲ ታክስታት ኣብ ዝቕመጥሉ ወይ ነባር ታክስታት ኣብ ዝልወጡሉ እዋን መሰረት ናይ'ቲ ታክስ ተመሳሳልን ዝተወሃሃደን ምኻኑ ንምርግጋፅ ምስ ፌደራል መንግስቲ ክማኸር ኣለዎ፡፡

## 49. ድልየት ወፃኢ ሸርፊ

ናይ እቲ ክልል መንግስቲ ሸርፊ ወፃኢ ከድልዮ እንተሎ ሸርፊ ወፃኢ ንምንታይ ዓላማ ከምዝውዕል ምስ ዘርኢ እኹል መረዳእታ ንሚኒስቴር ገንዘብን ኢኮኖሚ ልምዓትን ከፍልጥ ኣለዎ ፡፡

## 50. ፀብፃብ ሒሳብ መንግስቲ

ፀብፃብ ሒሳብ መንግስቲ ኣብ መንጎ እቲ ክልልን ፌደራል መንግስትን ዝተገብሩ ምንቅስቓሳት ፋይናንስን ናይ'ቲ ክልል ኩነታት ፋይናንስ ዘርኢ ናይ'ቲ በጀት ዓመት ናይ መወዳእታ ፀብፃብ

3. የክልሉ መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚጠይቀውን በማሟላት እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን ፎርም በመከተል በየወሩ በየሩብ ዓመቱ በየግማሽ ዓመቱ እና በየዓመቱ የፋይናንስ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል። ይህም ሪፖርት የክልሉን ገቢዎችና ወጪዎች ምንጫቸው እና በሂሣብ መለያ ቁጥሮች በመለየት ያላቸውን ጥሬ ገንዘብ ያልተከፈለውን ዕዳ መጠንና የሥራ አፈፃፀማቸውን የሚያሳይ መሆን አለበት።

## 48. የታክስ ውህደት

በክልሉ መንግሥት አዳዲስ ታክሶች በሚጣሉበት ወይም ነባር ታክሶች በሚለወጡበት ግዜ የታክስ መሠረቱ ተመሳሳይ እና የተዋሃደ መሆኑን ለማረጋገጥ ከፌደራል መንግስት ጋር ምክክር መደረግ አለበት።

## 49. የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት

የክልሉ መንግስት የውጭ ምንዛሪ ሲያስፈልግ የውጭ ምንዛሪው ለምን ዓላማ እንደሚውል ከሚያሳይ በቂ መረጃ ጋር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማሳወቅ አለበት፡፡

## 50. የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት

የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት በክልሉና በፌዴራል መንግስት መካከል የተደረጉትን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች እና የክልሉን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ የበጀት ዓመቱን የመጨረሻ ሪፖርት

www.abyssinialaw.com



ብዝተጠቓለለን ዝተነፃፀረን መልክዑ ዝሕዝ ኽኸውን አለዎ።

## 51. ምርመራ ሒሳብ

ቤት ፅሕፈት ዋና ኦዲተር ናይ'ቲ ክልል ከም ሓደ ስሩዕ ፕሮግራም ኦዲት መንግስቲ እቲ ክልል ምስ ፌደራል መንግስቲ ዝገብሮ ምንቅስቓስ ፋይናንስ ዝምልከቱ መዛግብቲ ይምርምር።

# ክፍሊ ዓሰርተ

# ሒሳብ መንግስቲ

## 52. ኣቀራርባ ሒሳብ መንግስቲ

ብመሰረት ኣዋጅ ቁፅሪ 172/2002 ዓንቀፅ 55 (3) መሰረት ስራሕ ፈፃሚ እቲ ክልል ብቐጥታ ተፀዋዕቲ ዘይኾኑ ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ ፀብፃብ ምርመራ ሒሳቦም ምስ ፀብፃብ ኣፈፃፅማ ስራሕ ብምትእስሳር ንዝምልከቶ ቀዋሚ ኮሚቴ ቤት ምኽርን ስራሕ ፈፃሚ እቲ ክልል ዘቕርብዎ ተፀዋዕቲ ብዝኾንሎም ናይ'ቲ ክልል ቢሮታት ኣቢሎም ይኸውን፡፡

## 53. ምዕፃው ሒሳብ መንግስቲ

ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ እቲ በጀት ዓመት ምስተወደአ ኣብ ውሽጢ ሰለስተ ወርሒ ሒሳቦም ዓፂዮም ብዋና ኦዲተር ናይ'ቲ ክልል ንክምርመር ሒሳብ ሪፖርቶም ከቕርቡ ኣለዎም፡፡

በተጠቃለለና በተነፃፀረ መልኩ የሚይዝ መሆን አለበት።

## 51. የሂሳብ ምርመራ

የክልሉ ዋናው ኦዲተር መስሪያቤት እንደ አንድ መደበኛ የኦዲት ፕሮግራም የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስት ጋር ያደረገውን የፋይናንስ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መዛግብትን ይመረምራል።

# ክፍል አሥር

# የመንግሥት ሂሳብ

## 52. የመንግስት ሂሳብ አቀራረብ

በኣዋጅ ቁፅር 173/2002 አንቀፅ 55(3) መሠረት ለክልሉ ስራ አስፈፃሚ በቀጥታ ተጠሪ ያልሆኑ የመንግስት መስሪያቤቶች የሂሳብ ምርመራ ሪፖርታቸውን ከሥራ ኣፈፃፀም ሪፖርት ጋር በማቀናጀት ለክልሉ ምክር ቤት ቀዋሚ ኮሚቴ እና ስራ አስፈፃሚ የሚያቀርቡት ተጠሪ በሆኑባቸው የክልሉ ቢሮዎች ኣማካኝነት ይሆናል።

## 53. የመንግስት ሂሳብን ስለመዝጋት

የመንግስት መስሪያቤቶች የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን ዘግተው በክልሉ ዋናው ኦዲተር እንዲመረመር የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡

www.abyssinialaw.com



## ክፍሊ ዓሰርተ ሓደ

## ውሽጢ ኦዲት

### 54. ስልጣን ውሽጢ ኦዲት

ውሽጢ ኦዲት ኣብያተ ፅዮ መንግስቲ ዝኾነ ናይ ቤት ፅዮኦም ፋይናንስ፣ ንብረትን ምንቅስቓስ ስራሕን ኦዲት ንምግባር ወሰን ዘይብሉ ስልጣን ኣለዎም፡፡

### 55. ሓላፍነትን ተግባርን ውሽጢ ኦዲት

1. ውሽጢ ኦዲት ኣብያተ ፅዮ መንግስቲ ነናይ ቤት ፅዮኦም ናይ ሓገዝ፣ ልቓሕን ውሽጢ ኣታዊን ዝሓውስ ፋይናንስን ስራሕን ኦዲት ይገብሩ፣
2. ትልሚ ስራሕ ኦዲት ቀፃሊ በጀት ዓመት ነንቤት ፅዮኦም ላዕለዋይ ሓላፊ ኣቕሪቦም ክፀድቕ ይገብሩ፡፡ ዝፀደቐ ትልሚ'ውን ነቲ ቢሮ የፍልጡ፣
3. ፀብፃብ ውፅኢት ስራሕቲ ኦዲት ነንቤት ፅዮኦም ላዕለዎት ሓለፍቲ የቕርቡ፡፡ ብቕዳሕ'ውን ንቢሮ የፍልጡ፡፡ ብመሰረት ኣብ'ቲ ፀብፃብ ዝቐረበ ሓሳብ ንተግባራዊነት ውሳነ ቢሮ ሓላፊ ይከታተሉ፡፡ ውፅኢት ፀብፃብ ክትትል'ውን ንላዕለዋይ ሓላፊ እቲ ቤት ፅዮን ነቲ ቢሮን የቕርቡ፡፡



## ክፍል አሥራ አንድ

## የውስጥ ኦዲት

### 54. የውስጥ ኦዲት ስልጣን

የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት ማናቸውም የመሥሪያ ቤታቸውን የፋይናንስ፣ የንብረትና የሥራ እንቅስቃሴ ኦዲት ለማድረግ ያልተገደበ ሥልጣን ኣላቸው፡፡

### 55. የውስጥ ኦዲት ተግባርና ሓላፊነት

1. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የውስጥ ኦዲት የየመሥሪያ ቤታቸውን የዕርዳታ፣ብድርና የውስጥ ገቢን የሚጨምር የፋይናንስና የስራ ኦዲት ያደርጋሉ፣
2. የተከታዩን በጀት ዓመት የኦዲት ሥራ ዕቅድ ለየመሥሪያ ቤታቸው የበላይ ኃላፊ አቅርበው ያፀድቃሉ፣ የፀደቀውንም ዕቅድ ለቢሮው ያሳውቃሉ፣
3. ያከናወኑትን የኦዲት ውጤት ለየመሥሪያ ቤታቸው የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ በግልባጩም ለቢሮው ያሳውቃሉ፡፡ በሪፖርቱ በቀረበው ሓሳብ መሠረት የቢሮ ኃላፊው የሰጠው ውሳኔ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላሉ፡፡ የክትትሉንም ውጤት ሪፖርት ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለቢሮው ያቀርባሉ፡፡

www.abyssinialaw.com



## ክፍሊ ዓሰርተ ክልተ

## ምጥፋእ ገንዘብን ንብረትን መንግስቲ

### 56. ምርመራ ምክያድ

1. ንብረትን ገንዘብን መንግስቲ ብዛዕባ ምጥፍኡ ወይ ምጉዳሉ ብዝኾነ ይኹን መልክዑ ኣብ ዝቐርበ ፀብፃብ ሰራሕተኛታት ቤት ዕዮ መንግስቲ ምሉእ ምትሕብባር ሃልዩዎ ዝተማልአ ምርመራ ክግበር አለዎ።
2. ካብ ገበን ወፃኢ ዝኾኑ ብጀካ ደቀቅትን ምስ ስራሕ ዝተተሓሓዙን ጥፍኣታት ሰራሕተኛታት መንግስቲ ተጠርጠርቲ ዝኾኑሉ ገበን ግዕዝይና ተፈፂሙ ኣብ ዝተረኸበሉ እዋን ናብ ናይ'ቲ ክልል ኮሚሽን ስነ-ምግባርን ፀረ-ግዕዝይናን ሪፖርት ክግበር ኣለዎ።
3. በዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተመልከተ ሕሉው ኮይኑ ኣብ ውሽጢ ቤት ዕዮ መንግስቲ ዝተፈፀመ ጥፍኣት ገበን ግዕዝይና እንተዘይኮይኑ እቲ ዋኒን ሽዑ ንሽዑ ንፖሊስ ሪፖርት ክግበር ይግበኦ፡፡
4. ኣብ ቤት ዕዮ መንግስቲ ዝካየድ ቀዳማይ ብርኪ ምርመራ ምስ ምጥፋእ ገንዘብን ንብረትን መንግስቲ ዝተተሓሓዘ ጥፍኣት ተፈፂሙ እዩ ንምባል ዘኽእል ምኽንያት ምህላዉ ኣብ ምርግጋፅ ዝተወሰነ ይኸውን።

## ክፍል አሥራ ሁለት

## የመንግሥት ገንዘብና ንብረት መጥፋት

### 56. ምርመራ ማካሄድ

1. የመንግሥት ንብረትና ገንዘብ ስለመጥፋቱ ወይም ስለመጉደሉ በየትኛውም መልኩ በቀረበው ሪፖርት ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ሙሉ ትብብር ኖሮ የተሟላ ምርመራ መደረግ አለበት።
2. የወንጀል ተግባር ያልሆኑ አነስተኛና ከሥራ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ጥፋቶች የመንግስት ሠራተኞች ተጠርጣሪ የሆኑበት የሙስና ወንጀል ተፈፅሞ በሚገኝበት ጊዜ ለክልሉ ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት መደረግ አለበት።
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተመልከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የተፈፀመው ጥፋት የሙስና ወንጀል ካልሆነ ጉዳዩ ወዲያውኑ ለፖሊስ ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፣
4. በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚካሄደው የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ ከመንግሥት ገንዘብ ወይም ንብረት ከመጥፋት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ ላይ የተወሰነ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com



57. ምቕራብ ፀብፃብ

1. ዝኾነ ይኹን ሰራሕተኛ መንግስቲ ጥፍኣት ዝተፈፀመ ምዃኑ እንተፈሊጡ ወይ እንተጠርጢሩ ሽዑ ንሽዑ ንኽፍሊ ሓላፊኡ ሪፖርት ክገብር አለዎ። እቲ ሓላፊ'ውን ዝቐረበሉ ፀብፃብ ሽዑ ንሽዑ ንምምሕዳር ሓላፊ ብፅሑፍ ሪፖርት ክምዝተገበረ ክምኡ'ውን ናይ'ቲ ቤት ዕዮ ክፍሊታት ሕግን ኦዲትን ቅዳሕ'ቲ ፀብፃብ ዝበፅሖም ምዃኑ ምርግጋፅ ሓላፍነት አለዎ። ሓላፊ ምምሕዳር ድማ ንላዕለዋይ ሓላፊ ቤት ዕዩኡን ንሓላፊ እቲ ቢሮን ቅዳሕ እቲ ፀብፃብ ይልእኽ።
2. ዝኾነ ይኹን መንግስታዊ ቤት ዕዮ ጥፍኣት ከምዝተፈፀመ እንተፈልጡ ፀብፃብ ናይ ምግባር ሓላፍነት ዘለዎም ምዃኑ ንሰራሕተኛታቱ ክፍልጥ አለዎ።

57. ሪፖርት ስለማቅረብ

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ጥፋት መፈፀሙን ሲደርስበት ወይም ሲጠረጥር ወዲያውኑ ለክፍል ኃላፊው ሪፖርት ማድረግ አለበት። ኃላፊው የቀረበለት ሪፖርት ወዲያውኑ ለአስተዳደር ኃላፊው በጽሁፍ ሪፖርት መደረጉን እንዲሁም የመ/ቤቱ የሕግ እና የኦዲት የሥራ ክፍሎች የሪፖርቱ ግልባጭ የደረሳቸው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። የአስተዳደር ኃላፊው ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለቢሮ ኃላፊው የሪፖርቱን ግልባጭ ይልካል።
2. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥፋት መፈፀሙን ካወቁ ሪፖርት የማድረግ ኃለፊነት ያለባቸው መሆኑን ለሠራተኞቹ ማሳወቅ አለበት።

58. መምርሒ

1. ቢሮ ፍትሒ ክልል ትግራይ ኣብ ዝተፈላለዩ ቢሮታትን ቤት ዕዮታትን እዚ ክልል ተመዲቦም ዝሰርሑ ወዳእቲ ነገር ዝምርሑሉ እቲ ቢሮ ባዕሉ ንዕኦም ዝቆፃፀረሉ መምርሒ ከውፅእ ይኽእል።
2. ገንዘብ መንግስቲ ዝእከበሉን ኣታዊ ዝግበረሉን ዝርዝር ስርዓት ዝውስን መምርሒ በቲ ቢሮ ይወፅእ።
3. ተኣካቢ ሒሳባትን ግቡኣትን ወይ ድማ ሕቶታት ይግበአንን ወይ ድማ ናይ'ዚኣቶም ክፍሊት ካብ መዝገብ ናይ ምስራዝ ኣፈፃፅማ ዝምራሕ ካብ እቲ ቢሮ ብዘውፀኦ መምርሒ መሰረት ይኸውን።

58. መመሪያ

1. የትግራይ ክልል ቢሮ ፍትህ በተሰያዩ ቢሮዎችና ፅህፈት ቤቶች ተመድበው የሚሰሩ ነገረ ፈጆች የሚመሩበት እና ቢሮው ራሱ እነሱን የሚቆጣጠርበት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።
2. የመንግስት ገንዘብ የሚሰበሰብበትን እና ገቢ የሚደረግበትን ዝርዝር ሥርዓት የሚወስን መመሪያ በቢሮው ይወጣል።
3. ተሰብሳቢ ሂሣቦችን ግዴታዎችን ወይም የይገባኛል ጥያቄዎችን ወይም የእነዚህ ክፍያ ከመዝገብ የመሰረዙ አፈፃፀም የሚመራው ከቢሮው በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

www.abyssinialaw.com





59. **ስጉምቲ ዲሲፕሊን**

1. ላዕለዋይ ሓላፊ ቤት ፅዮ መንግስቲ እኹል መረዳእታ ምህላው እንተረጋገፀ ከም ኣግባብነቱ ብናይ'ቲ ክልል መምርሒታት ቢሮ ሲቪል ሰርቪስ ወይ እቲ ቤት ፅዮ ብሕጊ ብዝተውሃቦ ስልጣን ኣብ ዘውፀኦ መምርሒ መሰረት ኣብ ልዕሊ'ቲ ዘጉደለ ሰራሕተኛ መንግስቲ ስጉምቲ ዲስፕሊን ይወስድ።
2. ብመሰረት ንኡስ ዓንቀፅ 1 ቤት ፅዮ መንግስቲ ዝወስዶ ስጉምቲ ዲስፕሊን ኣግባብ ብዘለዎም ካልኦት ኣካላት ካብ ዝውሰድ ዝኾነ ይኹን ተወሳኺ ስጉምቲ ኣየድሕንን።

60. **ምትካእ**

ገንዘብ መንግስቲ ብምጥፍኡ ምኽንያት ተወሳኺ ክፍሊት ዝሓትት ጉድለት ገንዘብ ምስ ዘጋጥም ላዕለዋይ ሓላፊ እቲ ቤት ፅዮ ወይ ብፅሑፍ ዝተመደበ ካልእ ሰራሕተኛ እንተፅድቕ ንተመሳሳሊ ተግባር ንኽውዕል ካብ'ቲ ዝተፈቐደ በጀት ኽፍሊት ንኽፍፀም ክሓትት አለዎ።

61. **ካዝናታት መንግስቲ**

1. ገንዘብ ተሓዚ ቤት ፅዮ መንግስቲ ብዘይ ፍቓድ እንተተረፉ፣ እንተሞይቱ ወይ ዓቕሚ እንተሰኢኑ እቲ ካዝና ብመራሒ ፋይናንስ እቲ ቤት ፅዮን ውሽጢ ኦዲት ብዝመርሕ ሓላፊን ይዕሸግ።
2. ላዕለዋይ ሓላፊ መንግስታዊ ቤት ፅዮ ብመሰረት መምርሒ እቲ ቢሮ ኣብ

59. **የዲሲፕሊን እርምጃ**

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በቂ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ እንደአግባብነቱ በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ መመሪያዎች ወይም መሥሪያ ቤቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት ጉድለቱ በሚመለከተው የመንግሥት ሠራተኛ ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ይወስዳል።
2. በንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚወስደው የዲሲፒሊን እርምጃ አግባብ ባላቸው ሌሎች አካላት ከሚወሰዱ ማንኛውም ሌላ እርምጃ አያድንም።

60. **መተካት**

የመንግሥት ገንዘብ በመጥፋቱ ምክንያት ተጨማሪ ክፍያን የሚጠይቅ የገንዘብ ጉድለት ሲያጋጥም የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በጽሑፍ የተመደበው ሌላ ሠራተኛ ሲያፀድቀው ለተመሳሳይ ተግባር እንዲውል ከተፈቀደው በጀት ላይ ክፍያ እንዲፈፀም መጠየቅ አለበት።

61. **የመንግሥት ካዝናዎች**

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤት ገንዘብ ያዥ ያለፈቃድ ሲቀር፣ ሲሞት ወይም ችሎታ ማነስ ሲኖረው ካዝናው በመሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ኃላፊ እና የውስጥ ኦዲት ኃላፊ ይታሸጋል።
2. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በቢሮው መመሪያ መሠረት በካዝናው ውስጥ

www.abyssinialaw.com



ውሽጢ እቲ ካዝና ዝርከብ ንምውሳንን ዝርዝሩ ንምድላውን ሽው ንሽው ኮሚቴ የጣይሽ።

3. እቲ ኮሚቴ ኣብ ቅድሚ ምስክራት እቲ ካዝና ብምኽፋት እቲ ቢሮ ዘውፅኦ መምርሒ ብዝእዝዞ መሰረት ምርመርኡ ምክያድን ብዛዕባ እቲ ዝረኸቦ ውፅኢት ሪፖርት ክገበርን ኣለዎ።

## 62. ጉድለት ምፅብፃብ

1. ዝኾነ ጉድለት ኣብ ውሽጢ ሒሳብ መንግስቲ ክፅብፀብ ኣለዎ።
2. ሓፈሻዊ ጉድለት ገንዘብ ዝኾነ ተመላሲ ከይሓወሰ እቲ ጉድለት ኣብ ዝተፈፀመሉ ናይ በጀት ዓመት ሒሳብ ይፅብፅብ ወይ እቲ ጉድለት ብእዋኑ ከይተፈልጠ እንተተርፍ ተግባራዊ ክኸውን ኣብ ዝኽእለሉ ዓመት ኣብ ናይቲ ክልል መንግስቲ ፀብፃብ ሒሳብ ክፅብፀብ ይግበር።
3. ጉድለታት እንትምለሱ እቲ ገንዘብ ኣብ ዝተመለሰሉ ዓመት በጀት ናይ መንግስቲ ሒሳብ ክፅብፀብ ኣለዎ።

## ክፍሊ ዓሰርተ ሰለስተ

## ዝተፈላለዩ ሕጋገታት

## 63. መዛግብቲ ዝፀንሕሉ ወሰን ግዜ

1. ዝኾነ ቤት ፅሕፈት መንግስቲ ንቤት ፅሕፈቱ ወይ ንናይ ደገ ኦዲተራት ንዝኾነ ዋኒን ብመረዳእታነት ዘድልዮ መዛግብትን መረዳእታታትን ፋይናንስ እኹል ጊዜ ከፀንሖ ኣለዎ።



የሚገኘውን ለመወሰንና ዝርዝሩን ለማዘጋጀት ወዲያወኑ ኮሚቴ ያቋቁማል።

3. ኮሚቴው በምስክሮች ፊት ካዝናውን በመክፈት ቢሮው የሚያወጣው መመሪያ በሚያዘው መሠረት ምርመራውን ማካሄድና ስላገኘውም ውጤት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

## 62. ጉድለት ሪፖርት ማድረግ

1. ማንኛውም ጉድለት በመንግሥት ሂሣብ ውስጥ ሪፖርት መደረግ አለበት።
2. በአጠቃላይ የገንዘብ ጉድለት ማንኛውም ተመላሽ ሳይጨመር ጉድለቱ በተፈፀመበት የበጀት ዓመት ሂሣብ ሪፖሪት ወይም ጉድለቱ በወቅቱ ሳይታወቅ ሲቀር ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት ዓመት በክልሉ መንግሥት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሪፖርት ይደረጋል።
3. ጉድለቶች ተመላሽ ሲደረጉ ገንዘቡ በተመለሰበት የበጀት ዓመት የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት መደረግ አለበት።

## ክፍል ኣሥራ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 63. መዛግብት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለውጭ ኦዲተሮች ለማንኛውም ጉዳይ በመረጃነት የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት በቂ ጊዜ ማቆየት አለበት።

www.abyssinialaw.com



2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተመልከተ እንተሃለወ'ውን ዝኾነ መረዳእታ ፋይናንስን መዛግብትን እንተንእሰ ንዓሰርተ ዓመታት ክፀንሑ ኣለዎም።

64. <u>ክፀንሑ ዘለዎም ዓይነታት መዛግብቲ</u>

በዚ ደንቢ ዓንቀፅ 63 መሰረት ክፀንሑ ዘለዎም መዛግብትን መረዳእታታትን ፋይናንስ እዞም ዝስዕቡ እዮም።

1. ስራሕ ፈፃሚ ናይ'ቲ ክልልን/ወይ ሓላፊ ናይ'ቲ ቢሮ ንኽፀድቕም ዝቐረቡ ዝኾኑ ይኹኑ ዋኒናት
2. ስጉምቲ ከምዝተወሰዱ ዘረድኡ ዝኾኑ ይኹኑ መረዳእታታት፣
3. ዋኒናት ፋይናንስ ብዝምልከት ዝተፅሓፉ ፅሑፋት
4. ዝኾኑ ይኹኑ ዝርዝር ምንቅስቓሳት ፋይናንስን ደገፍቲ ሰነዳትን፣
5. መዛግብቲ ቅብሊታትን ጥረ ገንዘብን ዝአመሰሉ ዝኾኑ ይኹኑ መሰረታዊ መዛግብቲ ፋይናንስን፣

65. <u>ብሜላታት ኤሌክትሮኒክስ ብዛዕባ ምጥቃም</u>

ናይ'ቲ ቢሮ ሓላፊ በቲ ኣዋጅን በዚ ደንቢ ዝተዘርገሐ ስርዓት ምምሕዳር መንግስታዊ ፋይናንስ ብዝበለፀ ቅልጡፍን ውፅኢታውን ክኸውን ንምግባር ዘኽእሉ ሜላታት ኤሌክትሮኒክስ ብስፍሓት ኣብ ጥቕሚ ንኽውዕሉ ይገብር።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም የፋይናንስ መረጃ መዛግብት ቢያንስ ለአሥር ዓመታት መቆየት አለባቸው።

64. <u>መቆየት ያለባቸው የመዛገብት ዓይነቶች</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 63 መሠረት መቆየት ያለባቸው የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው።

1. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ እና/ወይም የቢሮ ኃላፊ እንዲያፀድቃቸው የቀረቡ ማናቸውም ጉዳዮች፣
2. እርምጃ መወሰዱን የሚያስረዱ ማናቸውም ማስረጃዎች፣
3. የፋይናንስ ጉዳዮችን በተመለከተ የተፃፉ ፅህፎች፣
4. ማናቸውም ዝርዝር የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችና ደጋፊ ሰነዶች፣
5. የጥሬ ገንዘብና የደረሰኞች መዛግብትን የመሳሰሉ ማናቸውም መሠረታዊ የፋይናንስ መዛግብት።

65. <u>በኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ስለመጠቀም</u>

የቢሮ ኃላፊው በአዋጁና በዚህ ደንብ የተዘረጋው የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ይበልጥ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

66. **መሰጋገሪ ድንጋገ**

1. ብናይ'ቲ ክልል ስራሕ ፈፃሚ ናይ ፋይናንስ ምምሕዳር ደንቢ ቁፅሪ 11/1993 ንሰራሕተኛታት መንግስቲ ዝወሃብ ተፈፃሚነት ነዊሕ እዋን ልቓሕ እዚ ደንቢ ኣብ ስራሕ ካብ ዝወዓለሉ መዓልቲ ጀሚሩ ካብ ዝቑፀር ናይ ክልተ በጀት ዓመት እዋን ንደሓር ይቋረፅ፡፡

2. እዚ ደንቢ ኣብ ስራሕ ቅድሚ ምውዓሉ ዝተጀመሩ ምንቅስቓሳት ፋይናንስ ቅድም ክብል ኣብ ስራሕ ብዝነበረ ናይቲ ክልል ደንቢ ምምሕዳር ፋይናንስ መሰረት መፈፀምታ ይረኽቡ፡፡

67. **ሜላታት ምፅናሕ**

እዚ ቢሮ ብዛዕባ ኣተሓሕዛ መረዳእታታትን መዛግብትን ፋይናንስ ከከም ባህሪ እቲ ሰነድ ተታሒዙ ዝፀንሓሉ እዋን ዝውሰን ዝርዝር መምርሒ የውፅእ፡፡

68. **ዝተሰዓሩ ሕጊታት**

ቁፅሪ ደንቢ ፋይናንስ 11/1993 ፈፃሚ ስራሕ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ተሳዒሩ በዚ ደንቢ ተተኪኡ ኣሎ፡፡

69. **እዚ ደንቢ ዝፀንዓሉ እዋን**

እዚ ደንቢ ብቤት ምኽሪ ስራሕ ፈፃሚ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ካብ ዝፀደቐሉ ዕለት 11 ነሓሰ 2003 ዓ.ም ጀሚሩ ዝፀንዐ ይኸውን።

**ኣባይ ወልዱ**

**ፕረዚዳንት ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ**

66. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1. በክልሉ ስራ አስፈፃሚ የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 11/1993 ለመንግስት ሠራተኞች የሚሰጠው የረዥም ግዜ ብድር ተፈፃሚነት ይህ ደንብ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር የሁለት የበጀት ዓመት ጊዜ በኋላ ይቋረጣል፡፡

2. ይህ ደንብ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ከዚህ ቀደም በሥራ ላይ በነበረው የክልሉ ካቢኔ የፋይናንስ ደንብ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

67. **የማቆየት ዘዴዎች**

ቢሮው ስለፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብቶች አያያዝና እንደሰነዱ ባህርይ ተይዞ የሚቆይበትን ጊዜ የሚወሰን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

68. **የተሻሩ ሕጎች**

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስራ አስፈፃሚ የፋይናንስ ደንብ ቁጥር_____11/1993 ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል፡፡

69. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት ከፀደቀበት ነሐሴ 11/2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ኣባይ ወልዱ**

**የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕረዚዳንት**

www.abyssinialaw.com